## 1. መግቢያ

አብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብ የተሰማራውና የሀገሪቱም ኢኮኖሚ የተመሰረተው በግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ላይ በመሆኑ ግብርና በሀገሪቱ ሁለንተናዊ እድገት ላይ ከፍተኛ ድርሻ አለው፡፡

በአሁኑ ወቅት በሀገሪቱ ውስጥ ካሉት ዋና ዋና የግብርና ውጤቶችን ከሚያመርቱ የአምራች ክፍሎች መሀከል ሰፋፊና መካከለኛ የመንግስት ፣ የግል ንግድ የአምራቾች ህብረት ሥራ ማህበራት ሌሎች ድርጅቶች ያገኙበታል፡፡ እነዚህ ድርጅቶች በሀገሪቱ የግብርና ክፍለ ኢኮኖሚ ውስጥ ዘመናዊና የተሻሻለ የአሰራር ዘዴ የሚጠቀሙ በመሆናቸው በእርሻ መሬት አጠቃቀምና የተሻለ ምርት በማምረት እንዲሁም የተሻሻሉ የእንስሳት እርባታ ዘዴዎችን በመተግበር ሥራ ላይ ያላቸው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ ስለሆነም በሀገሪቱ ውስጥ ያለውን የምግብ እጥረት በማሻሻል በኩል ፣ በሀገሪቱ ውስጥ ለሚገኙ ኢንዱስትሪዎች ጥሬ ዕቃዎችን በማቅረብና የውጭ ምንዛሬ የሚያስገኙ ምርቶችን በማምረት እንዲሁም ጥሬ ግብአቶችን በማቅረብ ከግብርና ጋር ቀጥታ ግንኙነት ያላቸውን አግሮ ኢንዱስትሪዎች ለቋቋቋም የሚያደርጉት እገዛ ቀላል እንዳልሆነ ይገመታል፡፡ ስለዚህ ሰፋፊና መካከለኛ የመንግስት ፣ የግል ንግድ ፣ የአምራቾች የህብረት ሥራ ማህበራትና የሌሎች የድርጅቶች እርሻዎችን በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ውስጥ ስላላቸው ሚና ስታቲስቲካል መረጃዎችን መሰብሰብና አጠናቅሮ ለተጠቃሚ ማቅረብ ለፖሊሲና ዕቅድ አውጭዎች ዋነኛ ግብዓት በመሆን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕቅዶች ግባቸውን እንዲመቱ በማድረግ በኩል ወሳኝ ሚና አላቸው፡፡ በመሆኑም በ1997 በሚደረገው የሰፋፊና መካከለኛ እርሻዎች ቆጠራ በሀገሪቱ የሚገኙ በማንኛውም መንግስታዊ ፣ የግል ንግድና የአምራቾች ህብረት ሥራ ማህበር ውስጥ የሚካሄድ የግብርና እንቅስቃሴን በተመለከተ መሠረታዊ መረጃዎችን ይሰበሰባሉ፡፡

## 2. የ1997 ዓ.ም የሰፋፊና መካከለኛ የመንግስት ፣ የግል ንግድ ፣ የአምራቾች ህብረት ሥራ ማህበርና የሌሎች ድርጅቶች የግብርና ቆጠራ ዋና ዋና ዓላማዎች

ሀ. በሀገሪቱ በሚገኙ ሰፋፊና መካከለኛ የመንግስት ፣ የግል ንግድና የአምራቾች ህብረት ሥራ ማህበር እርሻዎች የተመረተውን አጠቃላይ የሰብል ምርት መጠንና በሰብል የተያዘ መሬት ስፋትን በክልልና በዞን ደረጃ ለማወቅና ለማወዳደር የሚያስችል መረጃ ለማግኘት

ለ. የሰፋፊና መካከለኛ የመንግስት፣ የግል ንግድ ፣ የአምራቾች ህብረት ሥራ ማህበራትና የሌሎች ድርጅት እርሻዎችን በተመለከተ ከዓመት ወደ ዓመት ያለውን የምርት መጠን የታረሰ መሬት ስፋት ለውጥ ለመገምገም የሚያስችል መረጃ ለማግኘት፡፡

ሐ. በክልልና በዞን ደረጃ ከሚገኙ ሰፋፊና መካከለኛ የመንግስት ፣የግል ንግድ፣ የአምራቾች ህብረት ሥራ ማህበርና ሌሎች ድርጅቶች እርሻዎች ከአንድ ሄክታር ላይ የሚገኘውን ምርት (Yield) ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅና ከግል ገበሬዎች ከአንድ ሄክታር ላይ ከሚገኘው ምርታማነት (Yield) ጋር ለማወዳደር የሚያስችል መረጃ ለማግኘት::

መ. በሰፋፊና መካከለኛ የመንግስት፣የግልንግድ፣የአምራቾች ህብረት ሥራ ማህበርና የሌሎች ድርጅቶች እርሻዎች የሚካሄደውን የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታን / ጥቅም ላይ የዋለ የማዳበሪያ ፣ ምርጥ ዘር ፣ የአካባቢ ዘር የፀረ ሰብል መድኃኒት ዓይነት ፣ መጠንና ዋጋ እንዲሁም የመስኖ አጠቃቀም ለማወቅ የሚያስችል መረጃ ለማግኘት::

ሠ. በሰፋፊና መካከለኛ የመንግስት፣የግልንግድ፣የአምራቾች ህብረት ሥራ ማህበርና የሌሎች ድርጅቶች እርሻዎች ውስጥ ያለውን የመሬት አጠቃቀም (በሰብል፣ በግጦሽ ፣ በህንጻ ፣ በመጋዘን ወዘተ የተያዘ መሬት) ለማወቅ ፣

ረ. በሀገሪቱ በሚገኙ በሰፋፊና መካከለኛ የመንግስት ፣ የግል ንግድ ፣ የአምራቾች የህብረት ሥራ ማህበራትና የሌሎች ድርጅቶች እርሻዎች ውስጥ ያሉትን የቤት እንስሳት ብዛት በዓይነት ፣ በዕድሜ ፣ በጾታና በአገልግሎት ዓይነት ለይቶ ለማወቅ እንዲሁም የንብ ቀፎዎችን ብዛት በዓይነትና የማር ምርት መጠንን ለማወቅ የሚያስችል መረጃ ለማግኘት

ሰ. በሰፋፊና መካከለኛ የመንግስት ፣ የግል ንግድ ፣ የአምራቾች ህብረት ሥራ ማህበራትና የሌሎች ድርጅቶች እርሻዎች ውስጥ የተሰማራውን የሰው ኃይል ብዛት በጾታና በሙያው ዓይነት ለይቶ ለማወቅ የሚያስችል መረጃ ለማግኘት::

በአጠቃላይ የመንግስት ፣ የግል ንግድና የአምራቾች ህብረት ሥራ ማህበራትና የሌሎች ድርጅቶች እርሻዎች ለጠቅላላ የሀገር ውስጥ የግብርና ውጤቶች ምርት የሚያደርገውን አስተዋጾ ለመገምገምና ሀገሪቱ ለምታዘጋጀው የአጭርና የረዥም ጊዜ የልማት ዕቅድ የሚረዱ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ነው:: በዚህ ቆጠራ እነዚህ እርሻዎችን በተመለከተ የሚሰበሰቡ መረጃዎች በተቻለ መጠን ስፋትና ጥልቀት እንዲኖራቸው ተደርጓል::

በዚህ መሠረት የሚሰበሰቡት መረጃዎች የሚከተሉት ይሆናል::

1. <u>የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ</u>

   ሀ. የዘር አጠቃቀም በሰብል ዓይነት

   ለ. የመስኖ አጠቃቀም በሰብል ዓይነትና በውሀ ምንጭ

   ሐ. የማዳበሪያ አጠቃቀምና መጠን በሰብልና በማዳበሪያ ዓይነት

   መ. የፀረ ሰብል ተባይ ፣ የፀረ አረምና የፀረ ሰብል በሽታ መድኃኒት አጠቃቀም በሰብል ዓይነት

   ሠ. የቋሚ ሰብሎች እግሮች

   ረ. የምርጥ ዘርና ምርጥ ዘር ያልሆነ (የአካባቢ ዘር) መጠንና ዋጋ

   ሰ. የፀረ-ሰብል መድኃኒት ዓይነት ፣ መጠንና ዋጋ

II. የመሬት አጠቃቀም

ሀ. በጊዜያዊ ሰብል ፣ የተያዘ መሬት ስፋት በሄክታር

ለ. በቋሚ ሰብል ፣ የተያዘ የመሬት ስፋት በሄክታር

ሐ. በግጦሽ ፣ የተያዘ መሬት ስፋት በሄክታር

መ. በእዳሪነት ያለ መሬት ስፋት በሄክታር

ሠ. በደን የተያዘ መሬት ስፋት በሄክታር

ረ. ከላይ ከተዘረዘሩት ውጭ /በሌላ/ የተያዘ መሬት ስፋት በሄክታር

በጊዜያዊ ሰብል ፣ በቋሚ ሰብል ፣ በግጦሽ ፣ በእዳሪነት ፣ በደንና እንደውም በሌላ ዓይነት የመሬት አጠቃቀም የተያዘ የመሬት ስፋት መጠን በሄክታር።

III. የታረሰ መሬት ስፋትና የተመረተ ምርት መጠን በሰብል ዓይነት

IV. የቤት እንስሳት ብዛት በአገልግሎት ዓይነት ፣ በዝርያ ፣ በዕድሜና በጾታ

V. የንብ ቀፎዎችብዛት ፣ ዓይነትና የማር ምርት መጠን

VI. የቤት እንስሳት በሽታና የህክምና ሁኔታ እንዲሁም የመኖ አጠቃቀም

VII. የቤት እንስሳት ዶሮዎችና ንብ የያዙ ቀፎዎች ብዛትና የተዋጽኦ ምርት

## 3. ጽንሰ ሀሳቦችና ፍችዎቻቸው

መረጃዎች ደረጃቸውና ጥራታቸው ተጠብቆ እንዲሰበሰቡ ለማድረግ አንድ ዓይነት ጽንሰ ሀሳብና ፍች መጠቀም ያስፈልጋል። በ1996 የኢትዮጵያ ግብርና ናሙና ጥናት የምንጠቀምባቸው ዋና ዋና ጽንሰ ሀሳቦችና ፍችዎቻቸው ከዚህ በታች ቀርበዋል።

መረጃ ሰብሳቢዎችም ሆኑ ሌሎች በቆጠራው የሚሳተፉ ሁሉ መመሪያውን በዝርዝር ማጤንና መረጃዎቹም በመመሪያው መሠረት መሰብሰባቸውን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል።

**1. ማሣ**

ማሣ ማለት በአንድ ወይም በድብልቅ የሰብል ዓይነት የተያዘ የመሬት አካል ነው።

**2. ሌላ የመሬት አጠቃቀም**

በሰብል ከተያዙ ማሣዎች ውጭ ያሉትን የመሬት ይዞታዎች የሚጠቃለሉበት የመሬት አካል ነው። ለምሣሌ እዳሪ መሬት ፣ የግጦሽ መሬት ፣ ደን መሬት የመሳሰሉትን ያጠቃልላል።

3. <u>የመኸር ሰብል</u>

ለዚህ ቆጠራ መኸር ሰብል ማለት <u>ከመስከረም 1 እስከ የካቲት 30 የሚሰበሰብ ማንኛውም ሰብል ነው፡፡</u> ሆኖም በአንዳንድ የደጋ ቦታዎች አንዳንድ የጥራጥሬ ሰብሎችን በተመለከተ የመኸር ወቅት እስከ መጋቢት ወር ሊራዘም ይችላል፡፡ የሰብሉ የዘር ወቅት ግን ከተጠቀሰው ጊዜ ውጪ ሊሆን እንደሚችል መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

4. <u>የበልግ ሰብል</u>

ለዚህ ቆጠራ የበልግ ሰብል ማለት ከላይ ከተጠቀሰው የመኸር ጊዜ ውጪ የሚሰበሰብ ማንኛውም ሰብል ነው፡፡

<u>ማስታወሻ</u>፡-

*የመኸርና የበልግ ሰብሎች ከላይ በተጠቀሱት ጊዜያት ውስጥ በዝናብ ፣ በውሃ ሸሽ ፣ በመስኖ . . . ወዘተ የሚመረቱ ሰብሎችን ችንደሚያጠቃልሉ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡*

5. <u>ጊዜያዊ ሰብለ</u>

ጊዜያዊ ሰብል ማለት ተዘርቶ ወይም ተተክሎ ከአንድ ዓመት ባነሰ ጊዜ ምርቱ የሚሰበሰብ ማንኛውም የሰብል ዓይነት ነው፡፡ ለምሣሌ ጤፍ ፣ በቆሎ ፣ . . . ወዘተ ወይም ተተክሎ ከአንድ ዓመት በላይ ቢቆይም ምርቱ ሲሰበሰብ ተክሉ የሚጠፋ ሰብል ጊዜያዊ ሰብል ይባላል ለምሣሌ ጎመን፡፡

6. <u>ቋሚ ሰብል</u>

ቋሚ ሰብል ማለት <u>የተተከለበትን ወይም የተዘራበትን መሬት ከአንድ ዓመት በላይ የሚይዝና ፍሬው ከተለቀመ በኋላ መዘራት ወይም መተከል ሳያስፈልገው በርከት ላሉ ዓመታት ፍሬ በመስጠት የሚቆይ የሰብል ዓይነት ነው፡፡</u> ለምሣሌ ቡና ፣ ብርቱካን ፣ ሻይ . . ወዘተ ናቸው፡፡ ነገር ግን ቋሚ ግጦሽ እንደቋሚ ሰብል አይቆጠርም፡፡

7. <u>ድብልቅ ሰብል</u>

ድብልቅ ሰብል ማለት በአንድ ማሣ ላይ የሚገኙ የጊዜያዊና የጊዜያዊ ሰብል ድብልቅ ወይም የጊዜያዊና የቋሚ ሰብል ድብልቅ ወይም የቋሚና ቋሚ ሰብል ድብልቅ ማለት ነው፡፡

8. <u>የዘር ዓይነት</u>

የዘር ዓይነቶች በሁለት ይከፈላሉ፡፡ እነርሱም በአካባቢ በዘልማድ ከሚመረተው ሰብል ለዘር የሚጠቀሙበትና ሌላው ከፍ ያለ ምርት የሚያስገኝ ጥራት ያለው የተሻሻለ /ምርጥ/ ዘር ናቸው፡፡

በኢትዮጵያ አብዛኛውን ጊዜ የተሻሻለ ወይንም /ምርጥ ዘር/ የሚመረተው በኢትዮጵያ ምርጥ ዘር ድርጅት በኩል ነው፡፡ በተጨማሪም መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ለምሣሌ ከግብርና ሚኒስቴር፣ ከመንግስት እርሻ ቡናና ሻይ ባለሥልጣን ፣ ከእርዳታ ሰጪ ድርጅቶች . . . ወዘተ የሚገኙ ጥሩ ምርት የሚሰጡ እንደምርጥ ዘር ይቆጠራሉ፡፡

ምርጥ ዘር የምንለው ለአንድ ጊዜ ብቻ ጥቅም ላይ ለማዋል በቀጥታ ከላይ ከተጠቀሱት ምንጮች የተገኘውን ነው::

9. **ፀረ ተባይ መድኃኒት**

ፀረ ተባይ ማለት ሰብልን በመብላት ምርት እንዲቀንስ ወይም እንዲጠፋ የሚያደርጉ ተባዮችን ለማጥፋት የሚጠቅም ማንኛውም ዓይነት የኢንዱስትሪ ውጤት የሆነ መድኃኒት ነው:: ለምሣሌ ፀረ ተምች . . . ወዘተ

10. **ፀረ በሽታ መድኃኒት**

ፀረ በሽታ ማለት የሰብል ልዩ ልዩ ክፍሎችን/ቅጠል ፣ ግንዱን ወይም ስሩን/በማጥቃት ምርት እንዲቀንስ ወይም እንዲጠፋ የሚያደርጉ ማናቸውም የሰብል በሽታዎችን ሊከላከል የሚችል የኢንዱስትሪ ውጤት መድኃኒት ነው::

11. **ፀረ አረም መድኃኒት**

ፀረ አረም ማለት ከባለይዞታው ቁጥጥር ውጪ በሰብል በተያዘው ማሣ ውስጥ በመብቀልና ለሰብሉ ምርታማነት አስፈላጊ የሆኑትን ሁሉ በመሻማት ሰብሉ እንዲጠፋ ወይም ምርቱ እንዲቀንስ የሚያደርጉትን እጽዋት የሚያጠፋ የኢንዱስትሪ ውጤት መድኃኒት ነው::

12. **መስኖ**

መስኖ ማለት ምርትን ለማምረት ወይም ለማሻሻል ሆነ ተብሎ በሰው ሠራሽ ዘዴ ማለትም በቦይ ፣ በቦቲ ውሀ በማጋዝ ፣ በኩሬና በመሳሰሉት በመጠቀም ማሳው በቂ ውኃ እንዲያገኝ ማድረግ ነው:: ሆኖም በዝናብና በጎርፍ መጥለቅለቅ የሚገኘው ውሀ እንደመስኖ አይቆጠርም::

13. **ሰብል ማምረት**

ድርጅቱ በእርሻ ሥራ ተሰማርቶ ሰብሎች /ቋሚ ፣ ጊዜያዊ ወይም ድብልቅ/ የሚያመርትና የሚተዳደር ከሆነ በሰብል ማምረት ተግባር ተሰማርቷል ይባላል:: ሰብሉን ለማምረት በአጋዥነት የሚጠቀምባቸው የቤት እንስሳት ለምሣሌ ለእርሻ ወይም ለትራንስፖርት /ማጓጓዣ/ ሚፀቀምቻ ጋማ ከብቶች . . . ወዘተ በዚሁ ሰብል ማምረት ተግባር ሥር ይጠቃለላሉ::

14. **ከብት እርባታ**

ድርጅቱ የዳልጋ ከብት ፣ በግ ፣ ፍየል ፣ ዶሮዎችና ንብ በተናጠል ወይም በጣምራ የሚያረባ ወይም የሚያደልብ ወይም በፀጉራቸው የሚጠቀም ከሆነ በከብት እርባታ ተሰማርቷል ይባላል:: ሆኖም የእርሻ በሬ ወይም ለማጓጓዣ የሚጠቀምባቸው የቤት እንስሳት ብቻ ቢኖሩት በከብት እርባታ እንደተሰማራ አያስቆጥረውም:: የቤት እንስሳት ቆጠራ በሚደረግበት ጊዜ ግን መረጃው በሚሰበሰብበት ቅጽ ላይ እንደሚመዘገቡ /እንደሚቆጠሩ መገንዘብ ያስፈልጋል::

15. <u>የቤት እንስሳት</u>

በዚህ ቆጠራ የቤት እንስሳት የዳልጋ ከብቶችን ፣ በጎችን ፣ ፍየሎችን ፣ ፈረሶችን ፣ በቅሎዎችን ፣ አህዮችንና ግመሎችን ያጠቃልላል::

16. <u>የዳልጋ ከብቶች</u>

የዳልጋ ከብቶች ሲባሉ ጥጃዎችን ፣ ጊደሮችን ፣ ላሞችን ፣ ወይፈኖችን ፣ ኮርማዎችንና በሬዎችን ያጠቃልላል::

17. <u>የአላባ ወቅት</u>

አንድ ላም ወተት መስጠት ከጀመረችበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አቆመችበት /ነጠፈችበት/ ድረስ ያለው ጊዜ የአለባ ወቅት ይባላል::

18. <u>የተዳቀሉ</u>

በዚህ ቆጠራ የተሻለ የወተት ምርት ወይም የሥጋ ምርት እንዲሰጡ ተብለው ከውጭ አገር ከመጡ ዝርያዎችና ከሀገር ውስጥ ዝርያዎች የተወለዱት የተዳቀሉ ይባላሉ::

19. <u>ያልተዳቀሉ</u>

በዚህ ቆጠራ ለወተት ወይም ለሥራ ምርት ባለይዞታው የሚጠቀምባቸውና ከሀገር ውስጥ ዝርያዎች ብቻ የተወለዱ የዳልጋ ከብቶችን ይመለከታል ያልተዳቀሉ ይባላሉ::

20. <u>ኩንታል</u>

ኩንታል ማለት መቶ ኪሎ ግራም የሚመዝን ክብደት ማለት ነው::

21. <u>ሄክታር</u>

ሄክታር ማለት 10000 (አስር ሺህ) ሜትር ካሬ ስፋት ያለው መሬት ማለት ነው:: ለምሣሌ 100 ሜትር በ100 ሜትር ወርድ ያለው መሬት አንድ ሄክታር ማለት ይሆናል::

22. <u>የወተት ላሞች</u>

የወተት ላሞች በቆጠራው ወቅት ወተት በመስጠት ላይ ያሉትን ፣ እርጉዝ የሆኑትን በተጨማሪም ከቆጠራው በፊት ወተት ሲሰጡ ነበሩና ወደፊት ይሰጣሉ ተብለው የሚገመቱትን ያጠቃልላል::

23. <u>የግጦሽ መሬት</u>

የድርጅቱ ይዞታ አካል ሆኖ ቆጠራው በሚካሄድበት ወቅት ድርጅቱ ለግጦሽ የሚገለገልበት መሬት ማለት ነው::

24. <u>እዳሪ መሬት</u>

እዳሪ መሬት ሰብል ሲመረትበት ቆይቶ መሬትን ለማዳበር ሆነ ተብሎ ቢያንስ ለአንድ የሰብል ዘመን ሳይታረስ የሚቆይ መሬት ነው::

25. <u>ዓምድ</u>

ዓምድ ማለት በቅጹ ወይም በመጠይቁ ለሚሰበሰቡት መረጃዎች አርዕስት የአርዕስቱ ማብራሪያና በአርዕስቱ ለሚጠየቁ ጥያቄዎች መልሶች ለመፃፊያ የተሰጠ ክፍት ቦታ

ነው። በዓምዶቹ መረጃዎች በቃላት ወይም በቁጥር ብቻ ወይም በሁለቱም ጥምር እንደአስፈላጊነቱ ሊሰፍሩ ይችላሉ።

**26.** ናሙና

ከአንድ አጠቃላይ ከሆነ ስብስብ (*POPULATION OR UNIVERSE*) ውስጥ የስብስቡን ባህሪዎች ሊይዝና ሊወክል የሚችል በሳይንሳዊ የአመራረጥ ዘዴ የሚመረጥ የስብስቡ አካል ናሙና ይባላል። ከአጠቃላይ ቆጠራ ጋር ሲነፃፀር ናሙና ወጪን ስለሚቀንስ የተወሰነ የሰው ኃይል ስለሚያስፈልገው ብዙ ጊዜ ስለማይፈጅና ለቁጥጥር ስለሚያመች ጠቀሜታ ያለው ነው።

**27.** የእርሻ ሥራ

የእርሻ ሥራ ማለት ማረስ ፣ መጠቅጠቅ ፣ ማበራየት ፣ ማጨድ . . . ወዘተ ማለት ነው። የቤት እንስሳት በእርሻ ሥራ ተሰማርተዋል የሚባለው የማረስ ወይም የመጠቅጠቅ ወይም የመውቃት ሌሎች ለእርሻ አጋዥ የሆኑ ሥራዎችን . . . ወዘተ የሰሩ እንደሆነ ነው።

**28.** የመንግስት እርሻ

በፌደራል ወይም በክልል መንግስት ወይም በፕራይቬታይዜህን ኤጀንሲ የሚተዳደርና በፌደራል መንግስት ወይም በክልል የኢንቨስትመንት ቢሮ የተመዘገበ ባለሙያዎችንና ሌሎች ሠራተኞችን ቀጥሮ በዘመናዊ የእርሻ ዘዴና መሣሪያዎች እየታገዘ የተለያዩ ሰብሎችንና ተክሎችን በማምረት የቤት እንስሳትን በማርባት ወይም በማድለብ ወይም ንብ በማነብ ሥራ የተሰማራና ምርቱን ለሀገር ውስጥ ፍጆታና ለውጭ ሀገር ለሽያጭ የሚያቀርብ መንግስታዊ ድርግት ነው።

**29.** የግል ንግድ እርሻ

በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ የግል ባለሀብቶች ህብረት የተቋቋመና የሚተዳደር በፌደራል ወይም በክልል ኢንቨስትመንት ቢሮ የተመዘገበ ወይም ከማንኛውም የመንግስት አካል ተመዝግቦ ህጋዊ ፈቃድ ያለው ባለሙያዎችንና ሌሎች ሠራተኞችን ቀጥሮ ወይም ባቋቋሙት ሰዎች ወይም ቤተሰብ የሚንቀሳቀሳ በዘመናዊ ወይም በባህላዊ የእርሻ ዘዴዎችና መሣሪያዎች እየታገዘ የተለያዩ ሰብሎችን በማምረት ወይም የተለያዩ የቤት እንስሳትን በማርባት ወይም በማድለብ ወይም ንብ በማነብ ሥራ ተሰማርቶ ምርቱን ለሀገር ውስጥ ፍጆታና /ለውጭ ሀገር ለሽያጭ የሚያቀርብ የግል ድርጅት ነው።

**30.** የአምራቾች ህብረት ሥራ ማህበር እርሻ

ከአንድ በላይ በሆኑ አምራች ገበሬዎች ህብረት የተለያዩ የግብርና ምርቶችን በማምረት የተገኘውን ምርትም ለአባላቱ በምርት ማምረት ሂደት በነበራቸው የሥራ አስተዋጽኦ  መጠን በዓይነት ወይም የተገኘውን አጠቃላይ ምርት በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ በሀገር ውስጥ ወይም በውጭ ሀገር በሚገኙ ገበያዎች በመሸጥ ገቢውን ለመከፋፈል በመስማማት በህግ የተቋቋመና በክልል ፣ በዞን ፣ በወረዳ በግብርና ቢሮ

የህብረት ሥራ ማህበራት ማደራጃ የተመዘገበና ፈቃድ ያገነ ማለት ነው፡፡ (በዚህ ትርጉም የአገልግሎት ሰጭ ህብረት ሥራ ማህበራት አይጠቃለሉም)

31. ሌሎች የድርጅት እርሻ (የት/ቤት ፣ የመንግስት መ/ቤት ፣ የሃይማኖት ድርጅቶች ፣ የወህኒ ቤቶችና መንግስታዊ ያልሆኑ እርዳታ ሰጭ ድርጅቶች እርሻ)

በት/ቤት ወይም በመንግስት መ/ቤት ወይም በሃይማኖት ድርጅቶች ወይም በወህኒ ቤቶች አስተዳደር ወይም መንግስታዊ ባልሆኑ እርዳታ ሰጭ ድርጅቶች . . . ወዘተ. የተቋቋመና በተለያዩ የግብርና ሥራ ዓይነቶች (በሰብል ማምረት ፣ በከብት ማርባትና ማድለብ ወይም በሁለቱም) ተሰማርተው የተለያዩ የግብርና ምርቶችን በማምረት ምርታቸውን ሙሉ በሙሉ ወይም አብዛኛውን የሚሸጡ እርሻዎችን ያጠቃልላል፡፡

## 4. በጥናቱ የሚሸፈኑ ሰብሎች ዝርዝር

### 1. ጊዜያዊ ሰብሎች

#### 1.1 የብርዕና የአገዳ ሰብሎች

ሀ. ገብስ
ለ. በቆሎ
ሐ. ዳጉሣ
መ. አጃ
ሠ. ማሽላ (ዘንጋዳ)
ረ. ጤፍ
ሰ. ስንዴ
ሸ. ሩዝ
ቀ. ሌሎች . . .ይገለጽ

#### 1.2 ጥራጥሬዎች

ሀ. ሽንብራ
ለ. ቦሎቄ (አደንጓሬ)
ሐ. ባቄላ
መ. ምስር
ሠ. አተር
ረ. ግብጦ
ሰ. አኩሪ አተር
ሸ. ጓያ
ቀ. አብሽ
በ. ሌሎች . . .ይገለጽ

#### 1.3 የቅባት ሰብሎች

ሀ. ተልባ
ለ. ለውዝ(ኦቾሎኒ)
ሐ. ኑግ
መ. ጎመን ዘር
ሠ. ሰሊጥ
ረ. ሱፍ
ሰ. ሌሎች . . .ይገለጽ

#### 1.4 ቅመማ ቅመም

ሀ. ጥቁር አዝሙድ
ለ. ነጭ አዝሙድ
ሐ. ሚጥሚጣ
መ. ዝንጅብል
ሠ. እርድ
ረ. በርበሬ
ሰ. ኮረሪማ
ሸ. ድንብላል
ቀ. ሌሎች . . .ይገለጽ

#### 1.5 አትክልት

ሀ. ቀይ ስር
ለ. ጥቅል ጎመን
ሐ. ካሮት
መ. አበባ ጎመን
ሠ. ነጭ ሽንኩርት

#### 1.6 ሌሎች

ሀ. ጥጥ
ለ. ሌላ ይገለጽ

ረ. የአበሻ ጎመን
ሰ. ሰላጣ
ሸ. ቀይ ሽንኩርት
ቀ. ቃሪያ
በ. ድንች
ተ. ዱባ
ቸ. ስኳር ድንች
ኀ. ቲማቲም
ነ. ጎደሬ
ኘ. ቆስጣ
አ. ፈሶሊያ(ፋጆሊ)
ከ. ሌሎች . . ይገለጽ

2. <u>ቋሚ ሰብሎች</u>

2.1 <u>ፍራፍሬ</u>

ሀ. ፖም
ለ. ሙዝ
ሐ. ወይን
መ. ሎሚ
ሠ. መንደሪን
ረ. ማንጎ
ሰ. ብርቱካን
ሸ. ፓፓያ
ቀ. አናናስ
በ. ትርንጎ
ተ. ዘይቱን
ቸ. ኮክ
ኀ. ከርቡህ (ሀብሀብ)
ነ. እንጆሪ
ኘ. ቴምር
ከ. አቡካዶ
ኸ. ፕለም

2.2 <u>ቅመማ ቅመም</u>

ሀ. ቁንዶ በርበሬ
ለ. ቀረፋ
ሐ. ቁርንፉድ
መ. ጥምዝ ቅመም
ሠ. ጤናዳም
ረ. ሄል
ሰ. እንስላል
ሸ. ሌሎች . . ይገለጽ

2.3 <u>የገንዘብ (ካሽ) ሰብል</u>

ሀ. ጫት
ለ. ቡና
ሐ. እንሰት
መ. ጌሾ
ሠ. ሸንኮራ አገዳ
ረ. ሻይ
ሰ. ትንባሆ
ሸ. ጉሎ
ቀ. ሌሎች . . ይገለጽ

*<u>ማሳሰቢያ</u>:-የሰፋፊና መካከለኛ እርሻዎች መረጃ በወረዳ ደረጃ ለመሰብሰብ የሚሄድ መረጃ ሰብሳቢ ሥራውን ከመጀመሩ በፊት አዲስ የተመሰረቱና የተቋቋሙ እርሻዎች ካሉ አጣርቶ ምዝገባውን በማካሄድ ሥራውን መጀመር እንደሚገባው ማስታወስ ተገቢ ነው::*

## 5. የምርት መጠን እንዲቀንስና እንዲጨምር የሚያደርጉ ምክንያቶች

### 5.1 የምርት መጠን እንዲቀንስ የሚያደርጉ ምክንያቶች

1. የዝናብ ብዛት
2. የዝናብ እጥረት
3. ፀረ አትክልት ተባዮች
4. ፀረ አዝርዕት ተባዮች
5. አረም
6. በረዶ
7. ውርጭ
8. ጎርፍ
9. የዱር አራዊት
10. አንበጣ
11. ወፍ
12. የዘር እጥረት (ማንኛውም)
13. የእርሻ መሬት ምርታማነት መቀነስ
14. በአካባቢው የፀጥታ ሁኔታ አለመረጋጋት
15. ሌሎች ምክንያት ናቸው፡፡

### 5.2 የምርት መጠን እንዲጨምር የሚያደርጉ ምክንያቶች

1. ማዳበሪያ መጠቀም
2. የተሻለ የአየር ሁኔታ መኖር
3. የተሻሻለ (ምርጥ) ዘር መጠቀም
4. ዘመናዊ (የተሻሻለ) የእርሻ መሣሪያ መጠቀም
5. ዘመናዊ የአሰራር (የአስተራረስ)ዘዴ መጠቀም
6. ሌሎች ምክንያቶች

## 6. መጠይቁን ለመሙላት የሚያስችል አጠቃላይ ማብራሪያዎች

ሀ. የመረጃዎች ምንጭ በእያንዳንዱ መጠይቅ ለቀረቡት መሞላት ያለባቸው ጥያቄዎች ድርጅቱ የሚገለገልባቸውን መዛግብትና ልዩ ልዩ ሰነዶችን መሠረት በማድረግ ነው፡፡ ለዚህ ዓይነት ተግባር የሚዉሉ መዛግብት ያለመኖር መረጃ ሰጪዎች ትክክል መልሶችን ለመስጠት እንዳይችሉ የማድረግ ተፅዕኖ አላቸው፡፡ ሆኖም ሁኔታው ሲረጋገጥ በተቻለ መጠን የተሟሉ መረጃዎችን በግምት ከመረጃው ሰጪው ለማግኘት መሞከር አስፈላጊ በመሆኑ ይህንኑ መተግበር የመረጃ ሰብሳቢው ኃላፊነት ነው፡፡

ለ. አንዳንድ ሰፋፊና መካከለኛ እርሻዎች ከአንድ በላይ የተለየ አድራሻ ያላቸው እርሻዎች ሊኖራቸው ስለሚችል ለእያንዳንዱ እርሻ የሚሞላ መጠይቅ በተናጠል መሆን ይኖርበታል፡፡

## 7. የቅጾች አሞላል መመሪያ

### የጊዜያዊና የቋሚ ሰብሎች የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ (በመኸር ወቅት) የቅጽ ሰ.መ.እ.ቆ 97/1 አሞላል፡፡

ይህ ቅጽ በሰብል ብቻ ፣ በከብት እርባታ ብቻ እንዲሁም በሁለቱም (በሰብልና ከብት እርባታ) ይተዳደራሉ ተብለው ለተጠቀሱት የመንግስት ፣ የግል ንግድ ፣ የአምራቾችና የሌሎች ድርጅት እርሻዎች በሙሉ ይሞላል፡፡ በዚህ ቅጽ በመንግስት ፣ በግል ንግድ ፣ በአምራቾችና በሌሎች ድርጅት እርሻ በዋናው መኸር የተመረቱ የጊዜያዊ ፣ የቋሚና የድብልቅ ሰብሎች ስምና በሌላ መሬት አጠቃቀም የተያዙ ማሣዎች ይመዘገባሉ፡፡ በመቀጠልም ሌሎች ከዚህ በታች የተገለጹት የመረጃ ዓይነቶች እያንዳንዱን የተመረተ የሰብል ዓይነትንና የመሬት አጠቃቀም በማስመልከት ለዚህ ተግባር በመንግስት ፣ በግል ንግድ ፣ በአምራቾች ህብረትና ሌሎች ድርጅት እርሻ ከሚመድበው ሠራተኛ ጋር በሚደረግ ቃለመጠይቅ መረጃዎች ተሰብስበው በዚህ ቅጽ በሚመለከተው ክፍልና ዓምድ ይሞላሉ፡፡ የቅጽ ዝርዝር አሞላል ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ማስታወሻ 1- *በድብልቅ ሰብል የተያዙ ማሣዎች ከተገኙ የድብልቅ ሰብሎችን በነጠላ በመመዝገብ በክፍል 2 የተዘረዘሩት መረጃዎች በየአንጻራቸው እንደሚሰበሰብላቸው ማስታወስ አስፈላጊ ነው፡፡*

ማስታወሻ 2- *በዚህ የመረጃ ሰብሳቢዎች መመሪያ እርሻው ተብሎ የተጠቀሰው ሁሉ የሰፋፊና መካከለኛ የመንግስት (የግል ንግድ) የአምራቾች ህብረት ሥራ ማህበርና የሌሎች ድርጅቶች እርሻ ለማለት ነው፡፡*

## ክፍል 1 የአካባቢ መለያ

ዓምድ 1- ክልል

እርሻው የሚገኝበት ክልል ስም በተሰጠው ክፍት ቦታ ይሞላል፡፡

ዓምድ 2 - ዞን

እርሻው የሚገኝበት ዞን ስም በተሰጠው ክፍት ቦታ ይሞላል፡፡

ዓምድ 3- ወረዳ

እርሻው የሚገኝበት ወረዳ ስም በተሰጠው ክፍት ቦታ ይሞላል፡፡

ዓምድ 4- የእርሻው ስም

የእርሻው ስም ተጠይቆ በተሰጠው ክፍት ቦታ ይሞላል:: ስም ከሌለው የድርጅቱ ስም ይሞላል::

ዓምድ 5- እርሻው የሚገኝበት ቀበሌ ገ/ማህበር

እርሻው የሚገኝበት ቀበሌ ገበሬ ማህበር ስም በተሰጠው ክፍት ቦታ ይሞላል:::

ዓምድ 6- የእርሻው የይዞታ ዓይነት

የእርሻው የይዞታ ዓይነት ተጠይቆ የመንግስት ከሆነ ኮድ «1»፣ የግል ንግድ ከሆነ ኮድ «2» ፣ የአምራቾች ህብረት ሥራ ማህበር እርሻ ከሆነ ኮድ «3» ፣ የሌሎች ድርጅት እርሻ ከሆነ ደግሞ ኮድ «4» በተሰጠው ክፍት ቦታ ይሞላል:: የማረሚያ ቤት ፣ የሀይማኖት ድርጅቶች ፣ የት/ቤቶች ፣ የውጭ ድርጅቶችና የመሳሰሉት እርሻዎች በሙሉ የሌሎች ድርጅት እርሻ በሚለው ኮድ ውስጥ ይካተታል::

ዓምድ 7 - እርሻውን የሚያካሄደው ኢንቨስተር /ሥራ አስኪያጅ ስም/

እርሻውን የሚያካሄደው ኢንቨስተር ወይም ሥራ አስኪያጅ ስም ተጠይቆ በተሰጠው ክፍት ቦታ ይሞላል:: ሆኖም ከአንድ በላይ በሆኑ ግለሰቦች የሚመራ ድርጅት ከሆነ በዚህ ዓምድ የዋናው ሥራ አስኪያጅ ስም ተጠይቆ ይሞላል::

ዓምድ 8- የግብርናው ዓይነት

ድርጅቱ የተሠማራበት የግብርና ዓይነት ተጠይቆ ሰብል ማምረት ከሆነ ኮድ «1» ፣ በከብት እርባታ ከሆነ ኮድ «2» ፣ በሁለቱም ከሆነ ደግሞ ኮድ «3» በተሰጠው ክፍት ቦታ ይሞላል::

## ክፍል 2. የጊዜያዊና የቋሚ ሰብሎች የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ (በመኸር ወቅት

ዓምድ 1- ተራ ቁጥር

ተራ ቁጥር ከ01 በመጀመር ተሞልቷል::
ይሞላል::

ዓምድ 2- የጊዜያዊ (የቋሚ ሰብል ስም)

እርሻው በ1997 ዓ.ም ዋናው መኸር ያመረታቸው የጊዜያዊ ፣ የቋሚ ፣ የድብልቅ ሰብሎች ስም በተሰጠው ባዶ ቦታ ይመዘገባሉ:: በዚህ ኮድ

ተብሎ የተተወው ቦታ ለቢሮ ሥራ ብቻ ስለሚያገለግል ምንም አይሞላበትም::

<u>ማስታወሻ</u>:- *በድብልቅ የተያዙ ማሣዎች በየሰብል ዓይነቱ በነጠላ በዚሁ ክፍል የተዘረዘሩት መረጃዎች እንደሚሰበሰብላቸውመቋስታወስ ያስፈልጋል::*

ዓምድ 3- <u>የዘር / ችግኝ ዓይነት (ምርጥ ዘር ፣ ምርጥ ዘር ያልሆነ)</u>

እርሻው በ1997 ዓ.ም ዋናው መኸር ላመረታቸው ሰብሎች የተጠቀመው የዘር / ችግኝ ዓይነት ምርጥ ዘር ከሆነ እያንዳንዱን የጊዜያዊም ሆነ የቋሚ ሰብል አስመልክቶ በመጠየቅ ምርጥ ዘር ከሆነ ኮድ «1» ምርጥ ዘር ያልተጠቀመ ከሆነ ደግሞ ኮድ «2» ዓምዱ በተተወው ቦዶ ቦታ ይሞላል::

ዓምድ 4- <u>በመስኖ ዘዴ (ተጠቅመዋል ፣ አልተጠቀሙም)</u>

እርሻው በ1997 ዓ.ም ዋናው መኸር ያመረታቸውን ሰብሎች የተጠቀመው ለማልማት የመስኖ ዘዴ ተጠቅሞ ወይም አልተጠቀመ እንደሆነ እያንዳንዱን ሰብል አስመልክቶ በመጠየቅ ተጠቅሞ ከሆነ ኮድ «1» ያልተጠቀመ ከሆነ ደግሞ ኮድ «2» በዓምዱ በተተወው ባዶ ቦታ ይሞላል::

ዓምድ 5- <u>በዓምድ 4 ኮድ 1 ከተሞላ ውሃው የተገኘው</u>

በዚህ ዓምድ በዓምድ 4 ኮድ 1 ከተሞላ ለመስኖ የተጠቀመው ውሀ የተገነው ከየት እንደሆነ በመጠይቅ ከወንዝ ከሆነኮድ «1» ፣ ከሀይቅ ከሆነ ኮድ «2» በዓምዱ በተተወው ባዶ ቦታ ይሞላል::

ዓምድ 6- 10 <u>የማዳበሪያ አጠቃቀም</u>

ዓምድ 6- <u>ማዳበሪያ (ተጠቅመዋል = 1 ፣ አልተጠቀሙም = 2)</u>

እርሻው ያለማቸውን ሰብሎች ምርት ለማሻሻል በዓምድ 2 የተመዘገቡትን እያንዳንዱ ሰብል አስመልክቶ ማዳበሪያ መጠቀም አለመጠቀሙን በመጠየቅ ተጠቅሞ ከሆነ ኮድ «1» ያልተጠቀመ ከሆነ ደግሞ ኮድ «2» በዚህ ዓምድ በተተወው ቦታ ይሞላል::

ዓምድ 7- <u>ማዳበሪያ ከተጠቀሙ (የተፈጥሮ ፣ የኬሚካል ፣ ሁለቱም</u>

በዓምድ 5 እርሻው ማዳበሪያ በመጠቀሙ ኮድ «1» ተሞልቶ ከሆነ በዚህ ዓምድ የማዳበሪያው ዓይነት ይጠየቃል:: ጥቅም ላይ የዋለው የማዳበሪያ ዓይነት ተጠይቆ የተፈጥሮ ከሆነ ኮፍ «1» ፣ ኬሚካል ከሆነ ኮድ «2» ፣ ሁለቱም ዓይነት ከሆነ ደግሞ ኮድ «3» በዚህ ዓምድ በተተወው ባዶ ቦታ ይሞላል::

ዓምድ 8 እና 9 <u>ኬሚካል ማዳበሪያ ከሆነ</u>

ዓምድ 8- <u>ዓይነቱ</u>

እርሻው የተጠቀመው ማዳበሪያ የኬሚካል ከሆነ (በዓምድ 6 ኮድ «2» ወይም «3» ከተሞላ) የተጠቀመው የኬሚካል ማዳበሪያ ዓይነት ተጠይቆ ዩሪያ ከሆነ ኮድ «1» ፣ ዳፕ ከሆነ ኮድ «2» ፣ ሌሎች ከሆነ ኮድ «3» ፣ ዩሪያና ዳፕ ከሆነ ኮድ «4» ፣ ዩሪያና ሌሎች ከሆነ ኮድ «5» ፣ ዳፕና ሌሎች ከሆነ ኮድ «6» እንዲሁም ሁሉንም ዓይነት ከሆነ ደግሞ ኮድ «7« በዓምዱ ብተተወው ባዶ ቦታ ይሞላል::

<u>ማስታወሻ</u>:- *ነጭ የማዳበሪያ ዓይነት ዩሪያ ሲሆን ቡላ (ግሪይ) ደግሞ ዳፕ ነው::*

ዓምድ 9- <u>መጠን</u>

ዓይነቱ በዓድ 7 የተጠቀሰው ጥቅም ላይ የዋለው የኬሚካል ማዳበሪያ መጠን ተጠይቆ በኪሎ ግራምና ግራም በዐምዱ በተተወው ባዶ ቦታ ውስጥ ይሞላል::

ዓምድ 10- <u>ዋጋ</u>

እርሻው በዐምድ 8 መጠን የተሞላለት ማዳበሪያ ዋጋ በብርና በሣንቲም ምን ያህል እንደሆነ ተጠይቆ በዚህ ዓምድ በተተወው ቦዶ ቦታ ይሞላል::

ዓምድ 11- <u>የፀረ ሰብል ማጥፊያ መድኃኒት (ተጠቅመዋል ፣ አልተጠቀሙም)</u>

እርሻው በዐምድ 2 ያስመዘገባቸውን እያንዳንዱን ሰብል አስመልክቶ ፀረ ሰብል ማጥፊያ መድኃኒት ተጠቅሞ ከሆነ በመጠየቅ ተጠቅሞ ከሆነ ኮድ «1» ካልተጠቀመ ደግሞ ኮድ «2» በዚህ ዓምድ በተዘጋጀው ባዶ ቦታ ይሞላል::

ዓምድ 12 - 14 <u>የሰብል መበላሸት ደርሷል ወይ ?</u>

ዓምድ 12- <u>አዎ ፣ የለም</u>

እርሻው በዓምድ 2 ያስመዘገበውን እያንዳንዱን ሰብል አስመልክቶ ሰብሎቹ ተዘርተው በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ በነበሩበት ወቅት የሰብል መበላሸት ደርሶ ከሆነ በመጤቅ የሰብል መበላሸት ደርሶ ከሆነ ኮድ «1» ካልደረሰ ደግሞ ኮድ «2» በዚህ ዓምድ በተዘጋጀው ባዶ ቦታ ይሞላል::

ዓምድ 13- <u>ከተበላሸ አንድ ዋነኛ ምክንያት</u>

በዓምድ 10 የሰብል መበላሸት ደርሷል ተብሎ ኮድ «1» ከተሞላ በዚህ ዓምድ የብልሽቱ አንድ ዋነኛ ምክንያት ተጠይቆ በዐምዱ በተዘጋጀው ቦዶ

ቦታ ይመዘገባል:: የሰብል መበላሸት ዝርዝር ምክንያቶች በገጽ 11 የተሰጡ ስለሆነ ይህንኑ ይመልከቱ:: በዚህ ዓምድ ሥር ኮድ ተብሎ የተተወው ቦታ ለቢሮ ሥራ ብቻ ስለሚያገለግል ምንም አይሞላበትም::

ዓምድ 14- <u>የብልሽቱ መጠን በመቶኛ</u>

በዓምድ 11 በተገለፀው ምክንያት በሰብል ላይ ጉዳት ደርሶ የነበረ ከሆነ ብልሽቱ ያደረሰው የጉዳት መጠን በመቶኛ ተጠይቆ በዚህ ዓምድ ይሞላል:: ለምሣሌ እርሻው ሊያገኝ ከሚችለው የሰብል ምርት መጠን ሩብ ያህሉ በደረሰው ብልሽት ምክንያት ቀንሷል ቢል በዚህ ዓምድ በተዘጋጀው ባዶ ቦታ 25 ይሞላል ማለት ነው::

ዓምድ 15 እና 16 <u>የቋሚ ሰብሎች እግረ ብዛት</u>

ዓምድ 15- <u>ፍሬ / ምርት ለመስጠት ያልደረሱ</u>

የእርሻው በዓምድ 2 ያስመዘገባቸው ቋሚ ሰብሎችን እያንዳንዱን በተመለከተ ፍሬ / ምርት ለመስጠት የደረሱ እግሮች ብዛትን በመጠየቅ ቁጥሩ በዚህ ዓምድ በተዘጋጀው ባዶ ቦታ ይሞላል::

ዓምድ 16- <u>ፍሬ / ምርት ለመስጠት ያልደረሱ</u>

የእርሻው በዓምድ 2 ያስመዘገባቸውን ቋሚ ሰብሎች እያንዳንዱን በማስመልከት ፍሬ / ምርት ለመስጠት ያልደረሱ እግሮች ብዛትን በመጠየቅ ቁጥሩን በዓምዱ በተዘጋጀው ባዶ ቦታ ይሞላል::

***<u>ማስታወሻ</u>:- ቋሚ ሰብሎች ፍሬ / ምርት ለመስጠት የደረሱና ያልደረሱ ተብለው የሚለዩት በ1996 ዓ.ም ሰብል ዘመን ያሉበት ሁኔታን በተመለከተ ብቻ መሆኑ መታወቅ ይኖርበታል::***

## ክፍል 3. <u>ለምርጥ ዘር ፣ ለመስኖ ዘዴ - ለማዳበሪያና ፀረ ሰብል ማጥፊያ መድኃኒት ጥቅም ላይ የዋለበት የመሬት ስፋት (በመኸር ወቅት)</u>

ዓምድ 1- <u>የመስመር ቁጥር</u>

የመስመር ቁጥር ከ01 በመጀመር በተከታታይ ተሰጥቷል::

ዓምድ 2- <u>የጊዜያዊ / የቋሚ ሰብል ስም</u>

የሰፋፊና መካከለኛ የመንግስት / የግል ንግድ አምራቾች ህብረት ሥራ ማህበር እርሻው የመስኖ ዘዴ ፣ ማዳበሪያ ፣ ምርጥ ዘርና ፀረ ሰብል ማጥፊያ መድኃኒት የተጠቀመባቸው የጊዜያዊና የቋሚ ሰብሎች በሙሉ በመጠየቅ በዚህ ዓምድ በተዘጋጀው ባዶ ቦታ ይመዘገባሉ:: በዚህ ዓምድ ኮድ

ተብሎ በተተወው ባዶ ቦታ ለቢሮ ሥራ ብቻ የሚያገለግል በመሆኑ ምንም አይሞላበትም።

ዓምድ 3- <u>ምርጥ ዘር ስፋት በሄክታር</u>

እርሻው በክፍል 3 በዓምድ 2 ያስመዘገባቸውን ሰብሎች እያንዳንዱን በማስመልከት በክፍል 2 ዓምድ 3 ምርጥ ዘር መጠቀሙን በመግለጽ ኮድ «1» ከተሞላ በዚህ ዓምድ የመሬት ስፋቱ በሄክታር ተጠይቆ መጠኑ በዓምዱ በተዘጋጀው ባዶ ቦታ ይሞላል።

ዓምድ 4- <u>መስኖ ዘዴ</u>

እርሻው በክፍል 2 በዓምድ 5 መስኖ ዘዴ መጠቀሙን በመግለጽ ኮድ «1» የተሞላባቸውን ሰብሎች እያንዳንዱን አስመልክቶ በዚህ ዓምድ የመስኖ ዘዴ የተጠቀመበት ሰብል የሸፈነው የመሬት ስፋት በሄክታር ተጠይቆ መጠኑ በዚህ ዓምድ በተዘጋጀው ባዶ ቦታ ይሞላል።

ዓምድ 5-9 <u>ማዳበሪያ</u>

እርሻው በክፍል 2 በዓምድ 6 ማዳበሪያ መጠቀሙን በመግለጽ ኮድ «1» የተሞላባቸውን ሰብሎች እያንዳንዱን ሰብል አስመልክቶ በክፍል 2 ዓምድ 8 የተጠቀመው የማዳበሪያ ዓይነት ዩሪያና የተፈጥሮ ፣ ዳፕ ፣ ዩሪያና ዳፕ ወይም ሌሎች ከሆነ የመሬት ስፋቱ በሄክታር ተጠይቆ በቅደም ተከተል ከዓምድ 5 በተዘጋጁት ባዶ ቦታዎች ውስጥ ይሞላል።

ዓምድ 10 <u>የመድኃኒቱ ዓይነት (በኮድ)</u>

እርሻው በክፍል 2 በዓምድ 10 ፀረ ሰብል መድኃኒት መጠቀሙን በመግለጽ ኮድ «1» የተሞላባቸው ሰብሎች እያንዳንዱን በማስመልከት የተጠቀሙት የፀረ ሰብል ማጥፊያ መድኃኒት ዓይነትን በመጠየቅ ፀረ ተባይ ከሆነ ኮድ «1» ፣ ፀረ በሽታ ከሆነ ኮድ «2» ፣ ፀረ አረም ከሆነ ኮድ «3» ፀረ ተባይና ፀረ በሽታ ከሆነ ኮድ «4» ፀረ ተባይና ፀረ አረም ከሆነ ኮድ «5» ፀረ በሽታ እና ፀረ አረም ከሆነ ኮድ «6» እንዲሁም ሁሉም ዓይነት ከሆነ ኮድ «7» በዚህ ዓምድ ሥር ኮድ ተብሎ በተዘጋጀው ቦዶ ቦታ ውስጥ ይሞላል።

ዓምድ 11 <u>ፀረ ሰብል ማጥፊያ መድኃኒት</u>

እርሻው በዓምድ 10 ፀረ ሰብል ማጥፊያ መድኃኒት መጠቀሙን በመግለጽ ኮድ ከተሞላ በእያንዳንዱ መድኃኒት የተሸፈነው (ኮድ በተሞላለት መድኃኒት) የመሬት ስፋት በሄክታር ጠይቆ መጠኑ በዚህ ዓምድ በተዘጋጀው ባዶ ቦታ ይሞላል።

## ክፍል 4. <u>የመሬት አጠቃቀም (በመኸር ወቅት)</u>

ዓምድ 1 <u>ተራ ቁጥር</u>

ተራ ቁጥር ከ01 በመጀመር በተከታታይ ተሰጥቷል።

ዓምድ 2 <u>የመሬት አጠቃቀም ዓይነት (በመኸር ወቅት)</u>

በዚህ ዓምድ በእርሻው ስር ሊገኙ ይችላሉ ተብለው የሚገመቱ የመሬት አጠቃቀሞች ተዘርዝረዋል። ሌሎች የሚለው የመሬት አጠቃቀም በእርሻው ሥር ሆነው በዓምዱ ከተዘረዘሩት የመሬት አጠቃቀሞች ውጭ የሆኑትን ሁሉ ያጠቃልላል። <u>ለምሣሌ</u>፡- በሠራተኛ መኖሪያ ቤቶች ፣ መጋዘኖችና በጋራዥ . . ወዘተ የተያዙ ቦታዎችን ያጠቃልላል።

በዚህ ዓምድ ሥር ኮድ ተብሎ የተተወው ባዶ ቦታ ለቢሮ ሥራ ብቻ ስለሚያገለግል ምንም አይሞላበትም።

ዓምድ 3 <u>ስፋት በሄክታር</u>

በዚህ ዓምድ በዐምድ 2 በተዘረዘሩት በእያንዳንዱ የመሬት አጠቃቀም የተያዘው የመሬት ስፋት በሄክታር ተጠይቆ መጠኑ በዓምዱ በተዘጋጀው ባዶ ቦታ ይሞላል።

ዓምድ 4 <u>ተራ ቁጥር</u>

ተራ ቁጥር ከ01 በመጀመር በተከታታይ ተሰጥቷል።

## ክፍል 5. <u>ለዘር የዋለ የምርጥ ዘርና ፣ ምርጥ ዘር ያልሆነ (የአካባቢ ዘር) መጠንና ዋጋ (በመኸር ወቅት)</u>

ዓምድ 1 <u>ተራ ቁጥር</u>

ተራ ቁጥር ከ01 በመጀመር ተሞልቷል።

ዓምድ 2 <u>የሰብሉ ስም</u>

በዚህ ዓምድ እርሻው ያመረታቸውን እያንዳንዱን ሰብል አስመልክቶ በክፍል 2 ዓምድ 3 የተገለጸው ጥቅም ላይ ያዋለው የዘር ዓይነት (ምርጥ ዘርና ምርጥ ዘር ያልሆነ) ሰብል ስም ተጠይቆ በዚህ ዓምድ በተዘጋጀው ባዶ ቦታ ይመዘገባል። በዚህ ዓምድ ሥር ኮድ ተብሎ የተተወው ቦዶ ቦታ ለቢሮ ሥራ ብቻ ስለሚያገለግል ምንም አይሞላበትም።

ዓምድ 3 እና 4 <u>ምርጥ ዘር</u>

ዓምድ 3 <u>መጠን</u>

እርሻው በዚህ ቅጽ ክፍል 2 ዓምድ 3 ምርጥ ዘር መጠቀሙን በመግለጽ ኮድ «1» የተሞላላቸው እያንዳንዱን ሰብል አስመልክቶ በዚህ ዓምድ የተጠቀመው

የምርጥ ዘር መጠንን በመጠየቅ መጠኑ በኪሎ ግራም በዓምዱ በተዘጋጀው ባዶ ቦታ ይሞላል::

ዓምድ 4 <u>ዋጋ</u>

እርሻው በዓምድ 3 ያስመዘገበውን የምርጥ ዘር መጠን ዋጋ በብርና በሣንቲም ምን ያህል እንደሆነ በመጠየቅ በዚህ ዓምድ በተዘጋጀው ባዶ ቦታ ይሞላል::

ዓምድ 5 እና 6 <u>ምርጥ ዘር ካልሆነ (የአካባ ዘር)</u>

እርሻው በዓምድ 3 ያስመዘገበውን የምርጥ ዘር መጠን ዋጋ በብርና በሣንቲም ምን ያህል እንደሆነ በመጠየቅ በዚህ ዓምድ በተዘጋጀው ባዶ ቦታ ይሞላል::

ዓምድ 5 <u>መጠን</u>

እርሻው በዚህ ቅጽ ክፍል 2 ዓምድ 3 ምርጥ ዘር አለመጠቀሙን በመግለጽ ኮድ «2» የተሞላላቸውን ሰብሎች እያንዳንዱን በማስመልከት በዚህ ዓምድ የተጠቀመው የዘር መጠን (የአካባ ዘር) ተጠይቆ በኪሎ ግራም በዓምዱ በተዘጋጀው ባዶ ቦታ ይሞላል::

ዓምድ 6 <u>ዋጋ</u>

እርሻው በዓምድ 5 ጥቅም ላይ እንዳዋለው ያስመዘገበው የአካባ ዘር መጠን ዋጋ በብርና በሣንቲም ምን ያህል እንደሆነ በመጠየቅ በዚህ ዓምድ በተዘጋጀው ባዶ ቦታ ይሞላል::

<u>ማስታወሻ</u>:- *እርሻው ሰብሎች ሁለቱንም የዘር ዓይነቶች ሊጠቀም ስለሚችል ይኸው ተጠይቆ በተገቢው ቦታ መሞላት::*

## ክፍል 6 <u>የፀረ ሰብል መድኃኒት ዓይነት ፣ መጠንና ዋጋ (በመኸር ወቅት)</u>

ዓምድ 1 <u>ተራ ቁጥር</u>

ተራ ቁጥር ከ01 በመጀመር ተሞልቷል::

ዓምድ 2 <u>የመድኃኒቱ ስም</u>

እርሻው ካመረታቸው ሰብሎች ፀረ ሰብል መድኃኒት መጠቀሙን በመግለጽ በቅጽ 97/1 ክፍል 2 ዓምድ 9 ኮድ «1» ላልተሞላላቸው:: በዚህ ዓምድ ደግሞ በጥቅም ላይ የዋለው መድኃኒት ስም ተጠይቆ በዓምዱ በተተወው ባዶ ቦታ ይመዘገባል:: የመድኃኒት ስም ሲባል የመድኃኒቱ መጠሪያ ሆነው የሚያገለግሉትን እንደማላታይን ፣ ዲዲቲ . . . ወዘተ በመባል የሚታወቁትን ማለት ነው:: በዚህ ዓምድ ኮድ ተብሎ የተተወው ባዶ ቦታ ለቢሮ ሥራ ብቻ ስለሚያገለግል ምንም አይሞላበትም::

ዓምድ 3-6 የፀረ ሰብል መድኃኒት ዓይነት ፣ መጠንና ዋጋ

ዓምድ 3 ዓይነቱ (ፀረ ተባይ ፣ ፀረ በሽታ ፣ ፀረ አረም

በዚህ ክፍል ዓምድ 2 የተሞላው የመድኃኒት ስም የግልጋሎት ዓይነት ተጠይቆ የመድኃኒቱ ግልጋሎት ፀረ ተባይ ከሆነ ኮድ «1» ፣ ፀረ በሽታ ከሆነ ኮድ «2» ፣ ፀረ አረም ከሆነ ደግሞ ኮድ «3» በዚህ ዓምድ በተዘጋጀው ባዶ ቦታ ይሞላል፡፡

ዓምድ 4 የመለኪያው ስም

በዚህ ክፍል በዓምድ 2 የተጠቀሰው መድኃኒት መጠን የተለካበት ስታንዳርድ መለኪያ ስም (ኪሎ ግራም ፣ ሊትር ፣ ቁጥር . . . ወዘተ) በመጠየቅ በዚህ ዓምድ በተዘጋጀው ባዶ ቦታ ፡፡ በዚህ ዓምድ ኮድ ተብሎ የተተወው ባዶ ቦታ ለቢሮ ሥራ ብቻ ስለሚያገለግል ምንም አይሞላበትም፡፡

ዓምድ 5 መጠን

እርሻው በዚህ ክፍል ዓምድ 4 የተገለጸውን የስታንዳርድ መለኪያ በመጠቀም በጥቅም ላይ ያዋለው መድኃኒት መጠን ተጠይቆ በዚህ ዓምድ በተዘጋጀው ባዶ ቦታ ይሞላል፡፡

ዓምድ 4 ዋጋ

እርሻው ጥቅም ላይ ያዋለው በዓምድ 5 መጠኑ የተገለጸው መድኃኒት ዋጋ በብርና በሣንቲም ምን ያህል እንደሆነ በመጠየቅ በዚህ ዓምድ ባዶ ቦታ ይሞላል፡፡

## ጠቅላላ የታረሰው መሬት ስፋትና የምርት መጠን (በመኸር ወቅት) የቅጽ ሰ.መ.እ.ቆ 97/1ለ አሞላል፡፡

ይህ ቅጽ በጥናቱ በሚሸፈኑት የመንግስት ፣ የግል ፣ የአምራቾች የህብረት ሥራ ማህበራትና የሌሎች ድርጅት እርሻዎች በዋናው መኸር ወቅት በሰብል ተሸፍኖ የነበረው መሬት ስፋትና የተገኘው የምርት መጠን በሰብል ዓይነት በቅደም ተከተል በሄክታርና በኩንታል የሚመዘገብበት/የሚሞላበት ነው፡፡ በድብልቅ ሰብል የተሸፈነ መሬት ከተገኘ እያንዳንዱ የድብልቅ ሰብል የሸፈነው መሬት ስፋትና የተገኘው ምርት መጠን በነጠላ በየአንፃራቸው መመዝገብ እንደሚያስፈልግ ማስታወስ ተገቢ ነው፡፡ ይህ ካልተቻለ እያንዳንዱ ድብልቅ ሰብል የሸፈነው የመሬት ስፋት የተገኘውን የምርት መጠን ድርሻን በመቶኛ መግለጽ ይቻላል፡፡

የቅጹ ዝርዝር አሞላል እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## ክፍል 1. <u>የአካባቢ መለያ</u>

ዓምድ 1-8

እነዚህን ዓምዶች ከቅጽ ሰ.መ.እ.ቆ 97/1ሀ ክፍል 1 ከዓምድ 1-8 ከተገለጸው የአሞላል መመሪያ ጋር ተመሳሳይ በመሆናቸው በማወራረስ ይሞላሉ::

## ክፍል 2. <u>ለጊዜያዊና ቋሚ ሰብሎች ጠቅላላ የታረሰው የመሬት ስፋትና የተገኘ/የሚገኝ የምርት መጠን (በመኸር ወቅት)</u>

ዓምድ 1 <u>ተራ ቁጥር</u>

ተራ ቁጥር ከ01 በመጀመር በቅደም ተከተል ተሞልቷል::

ዓምድ 2 <u>የሰብሉ ስም</u>

እርሻው በቅጽ ሰ.መ.እ.ቆ 97/1ሀ ክፍል 2 ዓምድ 2 ያስመዘገባቸው የሰብል ዓይነቶች በሙሉ ወደዚህ ዓምድ ይተላለፋል:: በዚህ ዓምድ ኮድ ተብሎ የተተወው ባዶ ቦታ ለቢሮ ሥራ ብቻ ስለሚያገለግል ምንም አይሞላበትም::

ዓምድ 3 <u>የማሣው ስፋት (በሄክታር)</u>

በዓምድ 2 በተጠቀሰው የሰብል ዓይነት የተያዘው የመሬት ስፋት በሄክታር ተጠይቆ በዚህ ዓምድ በተዘጋጀው ባዶ ቦታ ይሞላል::

ዓምድ 4 <u>ከአንድ ሄክታር የተገኘው (የሚገኘው)</u>
<u>የምርት መጠን (በኩንታል የምርታማነት ሁኔታ)</u>

በዓምድ 2 የተመዘገበውን የሰብል ዓይነት በማስመልከት ከእያንዳንዱ ሰብል በአንድ ሄክታር የተገኘው ወይም ሊገኝ ይችላል ተብሎ የተገመተው ምርት መጠን በኩንታል ተጠይቆ በዚህ ዓምድ በተዘጋጀው ባዶ ቦታ ይሞላል::

ዓምድ 5-7 <u>የሰብል መበላሸት ደርሷል ወይ ?</u>

ዓምድ 5. <u>አዎ /የለም</u>

እርሻው በዓምድ 2 ያስመዘገባቸውን እያንዳንዱን ሰብል አስመልክቶ የሰብል በመላሸት ደርሶ ከነበረ ተጠይቆ ኮድ « 1» ካልደረሰ ደግሞ ኮድ «2»በዚህ ዓምድ በተዘጋጀው ባዶ ቦታ ይሞላል::

ዓምድ 6. <u>ከተበላሸ አንድ ዋነኛ ምክንያት:-</u>

በዓምድ 5 የሰብል መበላሸት ደርሶ ነበር ተብሎ ኮድ «1» ከተሞላ በዚህ ዓምድ ለሰብሉ መበላሸት አንድ ዋነኛ ምክንያት ምን እንደሆነ በመጠየቅ በዓምዱ በተዘጋጀው ባዶ ቦታ ይመዘገባል:: በዚህ ዓምድ ሥር ኮድ ተብሎ የተተወው ባዶ ቦታ ለቢሮ ሥራ ብቻ ስለሚያገለግል ምንም አይሞላበትም::

ዓምድ 7 <u>የብልሽት መጠን በመቶኛ</u>

በዓምድ 6 በተገለጸው ምክንያት በሰብሌ ላይ ጉዳት ደርሶ ከነበረ የጉዳት መጠን መበቶኛ ተጠይቆ በዚህ ዓምድ በተዘጋጀው ባዶ ቦታ ይሞላል::

## <u>አስተያየት :-</u>

*የዚህን ክፍል አሞላል በሚመለከት የገጠመ ችግር ወይም ለመረጃ ጥራት ጠቃሚ የሆነ አስተያየት ካለ በዚህ ዓምድ በተዘጋጀው ባዶ ቦታ መስፈር ይኖርበታል::*

## <u>ማስታወሻ:-</u>

*ቋሚ ሰብሎችን በሚመለከት የምርት መጠን የሚጠየቀው የዓመቱን ማለትም የ1996 ምርት ዘመን በተመለከተ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል::*

የጊዜያዊ ሰብሎች የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ ( በበልግ ወቅት) የቅጽ ሰ.መ.እ.ቆ 97/2ሀ አሞላል::

## <u>ክፍል 1</u> <u>የአካባቢ መለያ</u>

<u>ዓምድ1-5</u> ክልል ዞን ቆጠራው የሚካሄድበት ክልል፣ ዞንና፣ እርሻውን የሚያካሂደው ኢንቨስተር/ ሥራ አስኪያጅ ስም ፣የእርሻው አይነት፣እርሻው የሚገኝበት ቀበሌ/ ገ/ማ ፣የእርሻው ስም እና የግብርናው አይነት በርዕሱ በቀረበው የዓምዶች ቅደም ተከተል ከቅጽ ሰ.መ.እ.ቆ 97/1ሀ ክፍል 1 ዓምድ 1-8 በመውሰድ ይሞላል::

## <u>ክፍል 2</u>. <u>የጊዜያዊ ሰብሎች የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ ( በበልግ ወቅት )</u>

የዚህ ክፍል አሞላል ከቅጽ ሰ.መ.እ.ቆ 97/1ሀ ክፍል 2 ጋር በአብዛኛው አንድ በመሆኑ የዚህኑ ክፍል አሞላ በማጤን በዚህ ክፍል የሚሰበሰቡ መረጃዎችን መሙላት ስለሚቻል ይህንኑ ተግባራዊ በማድረግ በዚህ ክፍል የሚሰበሰቡ መረጃዎችን ከመስክ ሰብስቦ መሙላት ከመረጃ ሰብሳቢው ይጠበቃል:: ሆኖም ይህ ክፍል ለበልግ ወቅት ሰብሎች ብቻ የሚያገለግል ስለሆነ ጊዜያዊ ሰብሎችን ቋሚ ሰብሎችን አይመለከትም::

## <u>ክፍል 3.</u> <u>ለምርጥ ዘር፣ለመስኖ ዘዴ፣ ለማዳበሪያና ፀር ሰብል ማጥፊያ መድኃኒት ጥቅም ላይ የዋለበት መሬት ስፋት /በበልግ ወቅት/</u>

የዚህ ክፍል አሞላል ከቅጽ ሰ.መ.እ.ቆ 97/1ሀ ክፍል 3 አሞላል ጋር ተመሳሳይ በመሆኑ የዚህን ክፍል የመረጃ አሞላል መመሪያ በመጠቀም በዚህ ክፍል የሚሞሉ መረጃዎችን በአግባቡ ማስፈር የመረጃ ሰብሳቢው ኃላፊነት ይሆናል::

## <u>ክፍል 4. የምርጥ ዘርና ምርጥ ዘር ያልሆነ ( የአካባቢ ዘር) መጠንና ዋጋ ( በበልግ ወቅት )</u>

የዚህ ክፍል አሞላል በቅጽ ሰ.መ.እ.ቆ 97/1ሀ ክፍል 4 አሞላ ጋር ተመሣሣይ ሲሆን ልዩነት በመኸርና በበልግ ተብሎ መከፈሉ ላይ ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ የቅጽ ስለዚህ የቅጽ ሰ.መ.እ.ቆ 97/1ሀ ክፍል 4 የአሞላል መመሪያን በመከተል ይህን ክፍል ማጠናቀቅ ከመረጃ ሰብሳቢው ይጠበቃል፡፡

## <u>ክፍል 5. የፀረ-ሰብል መድኃኒት ዓይነት ፣መጠን እና ዋጋ (በበልግ ወቅት)</u>

ይህ ክፍል የበልግ ወቅት የፀረ ሰብል መድኃኒት ዓይነት፣መጠንና ዋጋ የሚሞላበት ሆኖ አሞላሉ ግን በቅጽ ሰ.መ.እ.ቆ 97/1ሀ ክፍል 5 ከተሞላው ጋር አንድ ዓይነት በመሆኑ ይህንኑ ተከትሎ በዚህ ክፍል የሚፈለጉ መረጃዎች ጠይቆ መሙላት ያስፈልጋል፡፡

<u>ማስታወሻ:-</u>

***ለበልግ ወቅት ሌሎች የመሬት አጠቃቀሞችን በተመለከተ መረጃዎች ስለማይሰበሰቡ በዚህ ቅጽ ሌሎች የመሬት አጠቃቀሞችን የሚመለከቱ ጥያቄዎች አልተካተቱም፡፡***

## <u>ለጊዜያዊ ሰብሎች ጠቅላላ የተያዘው መሬት ስፋትና የምርት መጠን (በበልግ ወቅት) የቅጽ ሰ.መ.እ.ቆ 97/2ለ አሞላል፡፡</u>

## ክፍል 1. <u>የአካባቢ መለያ</u>

ከቅጽ ሰ.መ.እ.ቆ 97/2ሀ ክፍል 1 በማወራረስ ይሞላል፡፡

## ክፍል 2. <u>ጠቅላላ የታረሰው መሬት ስፋትና የምርት መጠን (በበልግ ወቅት)</u>

የዚህ ክፍል አሞላል ለቅጽ ሰ.መ.እ.ቆ97/1ለ ክፍል 2 ከተገለጸው የአሞላል መመሪያ ጋር ተመሣሣይ ሲሆን ልዩነታቸው ይህ ክፍል በበልግ ወቅት በሰብሎች የተሸፈነ ጠቅላላ የመሬት ስፋትና የተገኘ/ሊገኝ የሚችል የምርት መጠን የሚሞላበት መሆኑ ላይ ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ የቅጽ ሰ.መ.እ.ቆ97/1ለ አሞላል መመሪያን በመከተል በዚህ ክፍል የሚፈለጉ መረጃዎችን ጠይቆ መሙላት ያስፈልጋል፡፡

# <u>የቤት እንስሳት እና ዶሮዎችን ንብ የያዙ ቀፎዎች ብዛትና የተዋጽኦ ምርት የቅጽ ሰ.መ.እ.ቆ 97/3 አሞላል</u>

ይህ ቅጽ በቆጠራው በሚሸፈኑ ሰፋፊና መካከለኛ እርሻዎች በሙሉ የቤት እንስሳት፣ዶሮዎችና የንብ ቀፎዎች፣የወተት የእንቁላልና የማር ምርት መጠን፣የቤት እንስሳት በሽታ ሕክምና የመኖ አጠቃቀምን አስመልክቶ የሚሞላ ሲሆን ቆጠራው የሚደረገውም የካቲት 2/1997 ጀምሮ እስከ የካቲት 8/1997 ይሆናል:: ሆኖም ቃለመጠይቁ የሚመለከታቸው የካቲት 1/1997 የነበሩትን የቤት እንስሳት ዶሮዎች የንብ ቀፎዎችን ነው::

## ክፍል 1. <u>የአካባቢ መለያ</u>

*ዓምድ 1-8* ቆጠራው የሚካሄድበት ክልል፣ዞንና፣ወረዳ
በርዕሱ በተሰጠው ቅደም ተከተል መሠረት
ከቅጽ 97/1ሀ ክፍል 1 ከዓምድ 1-8 በማወራረስ ይመላሉ::

## ክፍል 2. <u>የቤት እንስሳት ዶሮዎች፣የንብ ቀፎዎችና የተዋጽኦ ምርት</u>

**2.1 <u>በየካቲት 1/1997 የቤት እንስሳትና ወይም ዶሮዎች ነበረዎት?</u>**

የእርሻው መልስ አዎን ከሆነ በተሰጠው ሣጥን ውስጥ ኮድ «1» በመሙላት መጠይቁን ማጠናቀቅ ያስፈልጋል:: አልነበረኝም ከሆነ ግን በተሰጠው ሳጥን ውስጥ ኮድ «2» በመሙላት የጥያቄው መጨረሻ ይሆናል:

### <u>የዳልጋ ከብቶች ብዛት በዕድሜ በአገልግሎትና በዝርያ (የካቲት 1/1997 የነበሩትን)</u>

1. <u>ጠቅላላ የዳልጋ ከብቶች ብዛት</u>

የካቲት 1/1997 ዓ.ም እርሻው የነበሩትን ጠቅላላ የዳልጋ ከብቶች ብዛትን በመጠየቅ በመለየት ብዛታቸውን በአንጻሩ ባሉት ክፍት ቦታ ውስጥ መሙላት ያስፈልጋል:: በተመሳሳይ መንገድ ድርጅቱ ካስመዘገባቸው ጠቅላላ የዳልጋ ከብቶች ውስጥ የወንድና የሴቶችን ቁጥር በመጠየቅ ብዛታቸው በትይዩ በተሰጠው ክፍት ቦታ ውስጥ ይሞላል::

***<u>ማስታወሻ:-</u>***

***<u>የተዳቀሉ</u> ስንል ንጹህ የውጭ ሀገር ዝርያ ያላቸውን እና የውጭ ሀገር ዝርያ ያላቸውን ከሀገር ውስጥ ዝርያ ጋር በማዳቀል የተወሰዱትን ሲሆን <u>የሀገር ውስጥ ዝርያ</u> ሲባል ደግሞ ያልተዳቀሉና ንጹህ የሀገር ውስጥ ዝርያ ያላቸውን ብቻ መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል::***

ሀ) <u>ከ6 ወር በታች</u>

በተራ ቁጥር 1 ከተመዘገቡት ጠቅላላ የዳልጋ ከብቶች ውስጥ ዕድሜያቸው ከ6 ወር በታች የሆኑትን ጠቅላላ ብዛት በመጠየቅ በአንጻራቸው ባሉት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባል:: ድርጅቱ ካስመዘገባቸው ጠቅላላ ዕድሜያቸው ከ6ወር በታች ከሆኑት ውስጥ የወንድና የሴቶች ቁጥር በመጠየቅ ብዛታቸውን በየአንጻራቸው ባሉት ክፍት ቦታዎች ውስጥ መሙላት ያስፈልጋል::

ለ) <u>6ወርና ከ1 ዓመት በታች</u>

በተራ ቁጥር 1 ከተመዘገቡት ጠቅላላ የዳልጋ ከብቶች ውስጥ ዕድሜያቸው 6 ወር እና ከ1 ዓመት በታች የሆኑትን ጠቅላላ ብዛት በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባል:: ድርጅቱ ካስመዘገባቸው ጠቅላላ ዕድሜያቸው ከ6 ወር እና ከ1 ዓመት በታች ከሆኑት ውስጥ የወንዶችና የሴቶች ቁጥር በመጠየቅ ብዛታቸውን በየአንጻራቸው ባሉት ክፍት ቦታዎች ውስጥ መሙላት ያስፈልጋል::

ሐ) <u>1 ዓመት ከ3 ዓመት በታች</u>

በተራ ቁጥር 1 ከተመዘገቡት ጠቅላላ የዳልጋ ከብቶች ውስጥ ዕድሜያቸው 1 ዓመትና ከ3 ዓመት በታች የሆኑትን ጠቅላላ ብዛት በመጠየቅ በአንጻራቸው በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባል:: ድርጅቱ ካስመዘገባቸው ጠቅላላ ዕድሜያቸው 1 ዓመትና ከ3 ዓመት በታች ከሆኑት ውስጥ የወንዶችና የሴቶችን ቁጥር በመጠየቅ ብዛታቸውን በየአንጻራቸው በተዘጋጁት ክት ቦታዎች ውስጥ መሙላት ያስፈልጋል::

መ) <u>3 ዓመትና ከ10 ዓመት በታች</u>

በተራ ቁጥር ከተመዘገቡት ጠቅላላ የዳልጋ ከብቶች ውስጥ ዕድሜያቸው 3 ዓመትና ከ10 ዓመት በታች የሆኑትን ጠቅላላ ብዛት በመጠየቅ በአንጻራቸው በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባል:: ድርጅቱ ካስመዘገባቸው ጠቅላላ ዕድሜያቸው ከ3 ዓመትና ከ10 ዓመት በታች ከሆኑት ውስጥ የወንዶችና የሴቶችን ቁጥር በመጠየቅ ብዛታቸውን በየአንጻራቸው በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ መሙላት ያስፈልጋል:: በተጨማሪም <u>በ«መ»የተመዘገበው የቀንድ ከብቶች ቁጥር የ«መ1» የ«መ2» የ«መ3» የ«መ5» እና የ«መ6» ድምር መሆኑን ማገናዘብ ያስፈልጋል</u>::

መ1) <u>ለሥጋ አገልግሎት የሚውሉ</u>

በ«መ» ከተከመዘገቡት ዕድሜያቸው 3 ዓመትና ከ10 ዓመት በታች ከሆኑት የዳልጋ ከብቶች ውስጥ ለዕርድ/ለሥጋ/አገልግሎት የሚውሉት ጠቅላላ ብዛት በአንጻራቸው በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባል:: ድርጅቱ ካስመዘገባቸው ጠቅላላ ለሥጋ የሚውሉት የዳልጋ ከብቶች የወንዶችና የሴቶችን

ቁጥር በመጠየቅ ብዛታቸውን በየአንጻራቸው ባሉት ክፍት ቦታዎች ውስጥ መሙላት ያስፈልጋል:: የሥጋ ከብቶች ሲባል ድርጅቱ ለራሱ የሥጋ ፍጆታም ሆነ የሥጋ ከብቶች ሲባል ድርጅቱ ለራሱ የሥጋ ፍጆታም ሆነ የሥጋ ከብት ነው ብሎ በማሰብ ለሽያጭ ያዘጋጀውን ወይም የሚያቀርበውን ያጠቃልላል::

መ2) <u>ለእርባታ አገልግሎት የሚውሉ</u>

በ«መ» ከተመዘገቡት ዕድሜያቸው 3 ዓመትና ከ10 ዓመት በታች ከሆኑት የዳልጋ ከብቶች ውስጥ ለእርባታ የሚውሉ ጠቅላላ ብዛትና እንዲሁም የወንድና የሴት ቁጥር ተጠይቆ በአንጻራቸው ባሉት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባል::ድርጅቱ ካስመዘገባቸው ጠቅላላ ለእርባታ አገልግሎት የሚውሉትን የዳልጋ ከብቶች ብዛታቸው ተጠይቆ በየአንጻራቸው በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ መሙላት ያስፈልጋል:: እርባታ ሲባል ድርጅቱ እንዲባዙለት በማሰብ ያስቀመጣቸው ሴትም ሆነ ወንድ የዳልጋ ከብቶችን ያጠቃልላል::

መ3) <u>የወተት ላሞች</u>

በ«መ» ከተመዘገቡት ዕድሜያቸው 3 ዓመትና ከ10 ዓመት በታች ከሆኑት የዳልጋ ከብቶች ውስጥ የወተት ላሞች ብዛት የወተት ከብቶች ብዛት ተጠይቆ በአንጻራቸው ባሉት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይሞላል:: ድርጅቱ ካስመዘገባቸው ጠቅላላ የወተት ላሞች በጾታ ብዛታቸው ተጠይቆ በየአንጻራቸው ባሉት ክፍት ቦታዎች ውስጥ መሙላት ያስፈልጋል:: የሚመዘገቡት የወተት ላሞች በቆጠራው ወቅት ወተት ሲሰጡ የነበሩት፣ወደፊት ሊሰጡ የሚችሉትና ክበድ/እርጉዝ የሆኑትን ጊደሮች ያጠቃልላል::

መ4) <u>ባለፉት 12 ራት ወተት የሰጡ ላሞች ብዛት</u>

በ «መ3» ከተመዘገቡት ውስጥ ባለፉት 12 ወራት ( ከየካቲት 2/1996-የካቲት 1/1997 ድረስ ) ስንት ላሞች ወተት እንደሰጡ ተጠይቆ ባሉት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባል::

መ5) <u>ለእርሻ አገልግሎት የሚውሉ</u>

በ« መ» ከተመዘገቡት ዕድሜያቸው 3 ዓመትና ከ10 ዓመት በታች ከሆኑት የዳልጋ ከብቶች ውስጥ ድርጅቱ በአብዛኛው ለእርሻ ሥራ የሚጠቀምባቸው ጠቅላላ ብዛት በመጠየቅ በአንጻራቸው በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባል:: በእርሻ ሥራ ላይ ሴት የቀንድ ከብቶችም ሊሰማሩ ስለሚችሉ ለሁለቱም ጾታዎች መረጃው መጠየቅ ይኖርበታል:: ድርጅቱ ካስመዘገባቸው ጠቅላላ ለእርሻ አገልግሎት የሚውሉ የዳልጋ ከብቶችን በጾታ በመለየት ብዛታቸው ተጠይቆ በየአንጻራቸው ባሉት ክፍት ቦታዎች ውስጥ መሙላት ያስፈልጋል:: በተጨማሪም የእርሻ ሥራ ሲባል ማረስን፣

መጠቅጠቅን ፣ መውቃትን ፣ ሌሎች ለእርሻ አጋዥ ሥራዎችን . . . ወዘተ እንደሚያጠቃልል መገንዘብ ያስፈልጋል::

መ6 <u>ለሌላ አገልግሎት የሚውሉ</u>

በ«መ» ከተመዘገቡት ዕድሜያቸው 3 ዓመትና ከ10 ዓመት በታች ከሆኑት የዳልጋ ከብቶች ውስጥ ከላይ ከተገለጹት /ለሥጋ፣ለወተትና ለእርሻ ሥራ ከሚውሉ /ውጭ ለሌላ አገልግሎት የሚውሉ ካሉ ጠቅላላ ብዛት በመጠየቅ ብዛታቸው በአንጻራቸው በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባል:: ድርጅቱ ካስመዘገባቸው ጠቅላላ ለሌላ አገልግሎት የሚውሉትን የዳልጋ ከብቶች በጾታ በመለየት ብዛታቸውን በመጠየቅ በየአንጻራቸው ባሉት ክፍት ቦታዎች ውስጥ መሙላት ያስፈልጋል::

<u>ማስታወሻ:-</u>

*ለሌላ አገልግሎት የሚውሉ ተብለው ከሚመዘገቡት ወተት ሰጥተው የሚያውቁ ጊደሮች ይጠቃልላሉ:: ለሌላ አገልግሎት የሚውሉት በዝርዝር በአስተያየት መልክ ይገለጽ::*

ሠ) <u>10 ዓመትና ከ10 ዓመት በላይ</u>

በተራ ቁጥር 1 ከተመዘገቡት ጠቅላላ የዳልጋ ከብቶች ውስጥ ዕድሜያቸው 10 ዓመትና ከ10 ዓመት በላይ የሆኑትን ጠቅላላ ብዛት በመጠየቅ በአንጻራቸው በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባል:: ድርጅቱ ካስመዘገባቸው ጠቅላላ 10 ዓመትና ከ10 ዓመት በላይ የሆኑትን የዳልጋ ከብቶች በጾታ በመለየት ብዛታቸውን በየአንጻራቸው በተዘጋጀው ክፍት ቦታዎች ውስጥ መሙላት ያስፈልጋል::

ረ. <u>ጠቅላላ :-</u> በጥያቄ ተራ ቁጥር ረ1፣ረ2፣ እና ረ3 የተዘረዘሩት የሀገር ውስጥ ዝርያ የውጭና የተዳቀሉ ዝርያ ያላቸው ዳልጋ ከብቶች ጠቅላላ ብዛት ተጠይቆ ይሞላል:: በተመዘገበው ጠቅላላ ብዛት በጾታ በመለየት ለየጾታው ይመዘገባል::

ረ1) <u>ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ዝርያ</u>

በተራ ቁጥር 1 ከተመዘገቡት ጠቅላላ የዳልጋ ከብቶች ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ዝርያ የሆኑትን ብቻ በመለየት ጠቅላላ ብዛታቸውን በመጠይቁ በተዘጋጀው ክፍት ቦታ ይሞላል:: በመቀጠልም ድርጅቱ ካስመዘገባቸው ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ዝርያ ከሆኑት ዳልጋ ከብቶች በጾታ በመለየት ብዛታቸውን በየጾታው አንጻር በተሰጡት ክፍት ቦታዎች ይሞላል::

ረ2) <u>ጠቅላላ የውጭ ዝርያ ያላቸው</u>

በተራ ቁጥር 1 ከተመዘገቡት ጠቅላላ የዳልጋ ከብቶች የውጭ ዝርያ ያላቸውን ብቻ በመለየት ጠቅላላ ብዛታቸውን በመጠየቅ በተሰጠው ክፍት ቦታ ይሞላል:: በመቀጠልም ድርጅቱ ካስመዘገባቸው ጠቅላላ የውጭ ዝርያ የሆኑ

ዳልጋ ከብቶችን በጾታ በመለየት ብዛታቸውን በመጠይቁ በየጾታቸው አንጻር በተዘጋጀው ባዶ ቦታ መሙላት::

ረ3) <u>ጠቅላላ የተዳቀሉ ዝርያ ያላቸው</u>

በተራ ቁጥር 1 ከተመዘገቡት ጠቅላላ የዳልጋ ከብቶች የተዳቀለ ዝርያ ያላቸውን ብቻ በመለየት ጠቅላላ ብዛታቸውን በመጠየቅ በተሰጠው ክፍት ቦታ ይሞላል:: በመቀጠልም ድርጅቱ ካስመዘገባቸው ጠቅላላ የተዳቀሉ ዝርያ ያላቸውን በጾታ በመለየት ብዛታቸውን በመጠየቅ በየጾታው አንጻር በተተወው ባዶ ቦታ መመዝገብ ይገባል::

## <u>የበጎች ብዛት በዕድሜና በአገልግሎት ( የካቲት 1/1994 የነበሩትን )</u>

2. <u>ጠቅላላ የበጎች ብዛት</u>

የካቲት 1/ 1996 ዓ.ም ድርጅቱ የነበሩት ጠቅላላ የበጎች ብዛት በመጠየቅ በአንጻራቸው በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይሞላል :: ድርጅቱ ያስመዘገባቸውን ጠቅላላ የበጎች ብዛት በጾታ በመለየት ብዛታቸውን በየአንጻራቸው ባሉት ክፍት ቦታዎች ውስጥ መሙላት ያስፈልጋል::

<u>ሀ) ከ6 ወር በታች</u>

በተራ ቁጥር 2 ከተመዘገቡት ጠቅላላ በጎች ውስጥ ዕድሜያቸው ከ6 ወር በታች የሆኑት ጠቅላላ ብዛት በመጠየቅ በአንፃራቸው ባሉት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባል:: ድርጅቱ ያስመዘገባቸውን ጠቅላላ ዕድሜያቸው ከ6 ወር በታች የሆኑትን በጎች በጾታ ጠይቆ በመለየት ብዛታቸውን በየአንጻራቸው በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ መሙላት ያስፈልጋል::

<u>ለ) 6 ወርና ከ1 ዓመት በታች</u>

በተራ ቁጥር 2 ከተመዘገቡት ጠቅላላ በጎች ውስጥ ዕድሜያቸው 6 ወርና ከ1 ዓመት በታች የሆኑት ጠቅላላ ብዛት በመጠየቅ በአንጻራቸው ባሉት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባል:: ድርጅት ካስመዘገባቸው ጠቅላላ ዕድሜያቸው 6 ወርና ከ1 ዓመት በታች የሆኑትን በጎች በጾታ በመለየት ብዛታቸውን በየአንጻራቸው በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ መሙላት ያስፈልጋል::

<u>ሐ) 1 ዓመትና ከ2 ዓመት በታች</u>

በተራ ቁጥር 2 ከተመዘገቡት ጠቅላላ በጎች ውስጥ ዕድሜያቸው 1 ዓመትና ከ2 ዓመት በታች የሆኑት ጠቅላላ ብዛት በመጠየቅ በአንጻራቸው ባሉት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባል:: ድርጅቱ ያስመዘገባቸውን ጠቅላላ ዕድሜያቸው 1 ዓመትና ከ2 ዓመት በታች የሆኑትን በጎች በጾታ በመለየት ብዛታቸውን በየአንጻራቸው በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ መሙላት ያስፈልጋል::

መ)  <u>2 ዓመትና ከ2 ዓመት በላይ</u>

በተራ ቁጥር 2 ከተመዘገቡት ጠቅላላ በጎች ውስጥ ዕድሜያቸው 2 ዓመትና ከ2 ዓመት በላይ የሆኑት ጠቅላላ ብዛት በመጠየቅ በአንጻራቸው በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባል። ድርጅቱ ያስመዘገባቸውን ጠቅላላ ዕድሜያቸው 2 ዓመትና ከ2 ዓመት በላይ የሆኑትን በጾታ በመለየት ብዛታቸውን በየአንጻራቸው በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ መሙላት ያስፈልጋል። በተጨማሪም በ «መ» የተመዘገበው የበጎች ቁጥር የ«መ1» ፣ የ«መ2»፣ የ«መ3» ፣እና የ«መ4» ድምር መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

መ1) <u>ለሥጋ አገልግሎት የሚውሉ</u>

ዕድሜያቸው 2 ዓመትና ከ2 ዓመት በላይ ከሆኑት ውስጥ ለሥጋ አገልግሎት የሚውሉ በጎች ጠቅላላ ብዛት በመጠየቅ በየአንጻራቸው በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባል። ድርጅቱ ያስመዘገባቸውን ጠቅላላ ለሥጋ አገልግሎት የሚውሉትን በጎች በጾታ በመለየት ብዛታቸውን በየአንጻራቸው በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ መሙላት ያስፈልጋል።

መ2) <u>ለፀጉር አገልግሎት የሚውሉ</u>

ዕድሜያቸው 2 ዓመትና ከ2 ዓመት በላይ ከሆኑት ውስጥ ለፀጉር ምርት የሚውሉ በጎች ጠቅላላ ብዛት በመጠየቅ በየአንጻራቸው በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይሞላል። ድርጅቱ ያስመዘገባቸውን ጠቅላላ ለፀጉር አገልግሎት የሚውሉትን በጎች በጾታ በመለየት ብዛታቸውን በየአንጻራቸው በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ መሙላት ያስፈልጋል።

መ3  <u>ለእርባታ አገልግሎት የሚውሉ</u>

ዕድሜያቸው 2 ዓመትና ከ2 ዓመት በላይ ከሆኑት ውስጥ ለእርባታ የሚውሉ በጎች ጠቅላላ ብዛት በመጠየቅ በየአንጻራቸው ባሉት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይሞላል። ድርጅቱ ያስመዘገባቸውን ጠቅላላ ለእርባታ አገልግሎት የሚውሉትን በጎች በጾታ በመለየት ብዛታቸውን በየአንጻራቸው በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ መሙላት ያስፈልጋል። እርባታ ሲባል ድርጅቱ እንዲባዙለት በማሰብ ያስቀመጣቸውን ሴትም ሆነ ወንድ በጎችን ያጠቃልላል።

መ4) <u>ለሌላ አገልግሎት የሚውሉ</u>

2 ዓመትና ከ2 ዓመት በላይ ከሆኑት በጎች ውስጥ ለሌላ አገልግሎት የሚውሉ ካሉ ጠቅላላ ብዛታቸው በመጠየቅ በየአንጻራቸው በተሰጡት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይሞላል። ድርጅቱ ያስመዘገባቸውን ጠቅላላ ለሌላ አገልግሎት የሚውሉትን በጎች በፆታ በመለየት ብዛታቸውን በየአንጻራቸው በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ መሙላት ያስፈልጋል። ይህም ከ «መ1»

እስከ «መ3» ከተጠቀሱት አገልግሎቶች ውጪ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል:: የአገልግሎቱም ዓይነት በአስተያየት መልክ ይገለጽ::

**ማስታወሻ:-**

1) ጠቅላላ = ወንድ ፣ ሴት የተዳቀሉ ፣ ያልተዳቀሉ
2) ተራ ቁጥር 3=ሀ፣ ለ፣ ሐ፣ መ
3) መ= መ1፣ መ2፣ መ3፣ መ4

   መሆኑን ማገናዘብ ያስፈልጋል::

ሠ) **በጥያቄ**:- ተራ ቁጥር ሠ1 ፣ሠ2፣ እና ሠ3 የተመዘገቡት በጎች ጠቅላላ ብዛት ተጠይቆ በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ይሞላል:: በመቀጠልም ከተመዘገቡት ጠቅላላ በጎች በጾታ በመለየት ብዛታቸውን በየጾታው አንጻር መሙላት ተገቢ ነው::

ሠ1 ) **ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ዝርያ**

በተራ ቁጥር 1 ከተመዘገቡት ጠቅላላ በጎች ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ዝርያ የሆኑት ብቻ በመለየት ጠቅላላ ብዛታቸውን በመጠይቁ በተሰጡት ክፍት ቦታ ይሞላል:: በመቀጠልም ድርጅቱ ያስመዘገባቸው ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ዝርያ ከሆኑት ዳልጋ ከብቶች በጾታ በመለየት ብዛታቸውን በየጾታው አንጻር በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ይሞላል::

ሠ2 ) **ጠቅላላ የውጭ ዝርያ ያላቸው**

በተራ ቁጥር 1 ከተመዘገቡት ጠቅላላ በጎች የውጭ ዝርያ ያላቸውን ብቻ በመለየት ጠቅላላ ብዛታቸውን በመጠየቅ በተሰጠው ክፍት ቦታ ይሞላል:: በመቀጠልም ድርጅቱ ካስመዘገባቸው ጠቅላላ የውጭ ዝርያ የሆኑ ዳልጋ ከብቶችን በጾታ በመለየት ብዛታቸውን በመጠይቁ በየጾታቸው በተዘጋጀው ባዶ ቦታ ይሞላል::

ሠ3) **ጠቅላላ የተዳቀሉ ዝርያ ያላቸው**

በተራ ቁጥር 1 ከተመዘገቡት ጠቅላላ በጎች የተዳቀለ ዝርያ ያላቸውን ብቻ በመለየት ጠቅላላ ብዛታቸውን በመጠየቅ በተሰጠው ክፍት ቦታ ይሞላል:: በመቀጠልም ድርጅቱ ካስመዘገባቸው ጠቅላላ የተዳቀሉ ዝርያ ያላቸውን በጾታ በመለየት ብዛታቸውን በመጠየቅ በየጾታው አንጻር በተዘጋጀው ባዶ ቦታ መመዝገብ ይገባል::

**ፍየሎች ብዛት በዕድሜና በአገልግሎት ( የካቲት 1/1997 የነበሩትን )**

**3. ጠቅላላ የፍየሎች ብዛት**

የካቲት 1/1997 ዓ.ም ድርጅቱ የነበሩት ጠቅላላ የፍየሎች ብዛት በመጠየቅ በአንጻራቸው በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይሞላል:: ድርጅቱ ያሰመዘገባቸውን ጠቅላላ ፍየሎች በጾታ በመለየት ብዛታቸውን በየአንጻራቸው በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ መሙላት ያስፈልጋል::

**ሀ) ከ 6 ወር በታች**

በተራ ቁጥር 3 ከተመዘገቡት ጠቅላላ ፍየሎች ውስጥ ዕድሜያቸው ከ6 ወር በታች የሆኑት ጠቅላላ ብዛት በመጠየቅ በአንጻራቸው ባሉት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባል:: ድርጅቱ ያስመዘገባቸውን ጠቅላላ ዕድሜያቸው ከ6ወር በታች የሆኑትን ፍየሎች በጾታ በመለየት ብዛታቸውን በየአንጻራቸው በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ መሙላት ያስፈልጋል::

**ለ) 6 ወርና ከ1 ዓመት በታች**

በተራ ቁጥር 3 ከተመዘገቡት ጠቅላላ ፍየሎች ውስጥ ዕድሜያቸው 6 ወርና ከ1 ዓመት በታች የሆኑት ጠቅላላ ብዛት በመጠየቅ በአንጻራቸው በተዘጋጀው ካርድ ኮለሞች ውስጥ ይመዘገባል:: ድርጅቱ ያስመዘገባቸውን ጠቅላላ ዕድሜያቸው ከ 6 ወርና ከ1 ዓመት በታች የሆኑትን ፋይሎች በጾታ በመለየት ብዛታቸውን በየአንጻራቸው በተዘጋጀው ክፍት ቦታዎች ውስጥ መሙላት ያስፈልጋል::

**ሐ) 1 ዓመትና ከ2 ዓመት በታች**

በተራ ቁጥር 3 ከተመዘገቡት ጠቅላላ ፍየሎች ውስጥ ዕድሜያቸው 1 ዓመትና ከ2 ዓመት በታች የሆኑት ጠቅላላ ብዛት በመጠየቅ በአንጻራቸው በተዘጋጀው ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባል:: ድርጅቱ ያስመዘገባቸውን ጠቅላላ ዕድሜያቸው ከ1 ዓመት እና ከ2 ዓመት በታች የሆኑትን ፍየሎች በጾታ በመለየት ብዛታቸውን በየአንጻራቸው በተዘጋጀው ክፍት ቦታዎች ውስጥ መሙላት ያስፈልጋል::

**መ) 2 ዓመትና ከ2 ዓመት በላይ**

በተራ ቁጥር 3 ከተመዘገቡት ጠቅላላ ፍየሎች ውስጥ ዕድሜያቸው 2 ዓመትና ከ2 ዓመት በላይ የሆኑት ጠቅላላ ብዛት በመጠየቅ በአንጻራቸው በተዘጋጀው ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባል:: ድርጅቱ ያስመዘገባቸውን ጠቅላላ ዕድሜያቸው ከ2 ዓመትና ከ2 ዓመት በላይ የሆኑትን በጾታ በመለየት

ብዛታቸውን በየአንጻራቸው በተዘጋጀው ክፍት ቦታዎች ውስጥ ሙሙላት ያስፈልጋል፡፡በተጨማሪም በ«መ» የተመዘገበው የፍየሎች ቁጥር የ«መ1»፣ የ«መ2»፣ የ«መ3»፣እና የ«መ4» ድምር መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

<u>መ1) ለሥጋ አገልግሎት የሚውሉ</u>

ዕድሜያቸው 2 ዓመትና ከ2 ዓመት በላይ ከሆኑት ውስጥ ለሥጋ የሚውሉ ፍየሎች ጠቅላላ ብዛት በመጠየቅ በአንጻራቸው በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባል፡፡ ድርጅቱ ያስመዘገባቸው ጠቅላላ ለሥጋ አገልግሎት የሚውሉን ፍየሎች በጾታ በመለየት ብዛታቸውን በየአንጻራቸው በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ መሙላት ያስፈልጋል፡፡

<u>መ2) የወተት ፍየሎች</u>

ዕድሜያቸው 2 ዓመትና ከ2 ዓመት በላይ ከሆኑት ውስጥ ድርጅቱ ወተት ይሰጡኛል ብሎ ያስቀመጣቸው ፍየሎች ብዛት በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይሞላል፡፡

<u>መ3) ለእርባታ አገልግሎት የሚውሉ</u>

ዕድሜያቸው 2 ዓመትና ከ2 ዓመት በላይ ከሆኑት ውስጥ ለእርባታ የሚውሉ ፍየሎች ጠቅላላ ብዛት በአንጻራቸው በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይሞላል፡፡ ድርጅቱ ያስመዘገባቸው ጠቅላላ ለእርባታ አገልግሎት የሚውሉን ፍየሎች በጾታ በመለየት ብዛታቸውን በየአንጻራቸው ባሉት ክፍት ቦታዎች ውስጥ መሙላት ያስፈልጋል፡፡

<u>መ4) ለሌላ አገልግሎት የሚውሉ</u>

2 ዓመትና ከ2 ዓመት በላይ ከሆኑት ፍየሎች ውስጥ ለሌላ አገልግሎት የሚውሉ ካሉ ጠቅላላ ብዛታቸው በተሰጡት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይሞላል፡፡ ድርጅቱ ያስመዘገባቸውን ጠቅላላ ለሌላ አገልግሎት የሚውሉ ፍየሎችን በጾታ በመለየት ብዛታቸውን በየአንጻራቸው ባሉት ክፍት ቦታዎች ውስጥ መሙላት ያስፈልጋል፡፡ ይህም ከ «መ1» እስከ «መ3» ከተጠቀሱት አገልግሎቶች ውጪ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ የአገልግሎቱም ዓይነት በአስተያየት መልክ ይገለጽ፡፡

ሠ. <u>ጠቅላላ</u>:- በጥያቄ ተራ ቁጥር ሠ1፣ ሠ2 እና ሠ3 የተመዘገቡት ፍየሎች ጠቅላላ ብዛት ተጠይቆ በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ይሞላል፡፡ በመቀጠልም የተመዘገቡትን ጠቅላላ በጎች በጾታ በመለየት ብዛታቸውን በየጾታው አንጻር መሙላት ተገቢ ነው፡፡

*ሠ1* *ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ዝርያ*

በተራ ቁጥር 1 ከተመዘገቡት ጠቅላላ ፍየሎች ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ዝርያ የሆኑትን ብቻ በመለየት ጠቅላላ ብዛታቸውን በመጠይቁ በተሰጡት ክፍት ቦታ ይሞላል:: በመቀጠልም ድርጅቱ ያስመዘገባቸው ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ዝርያ ከሆኑት ዳልጋ ከብቶች በጾታ ከብቶች በመለየት ብዛታቸውን በየጾታው አንጻር በተሰጡት ክፍት ቦታዎች ይሞላል::

*ሠ2* *ጠቅላላ የውጭ ዝርያ ያላቸው*

በተራ ቁጥር 1 ከተመዘገቡት ጠቅላላ ፍየሎች የውጭ ዝርያ ያላቸውን ብቻ በመለየት ጠቅላላ ብዛታቸውን በመጠየቅ በተሰጠው ክፍት ቦታ ይሞላል:: በመቀጠልም ድርጅቱ ካስመዘገባቸው ጠቅላላ የውጭ ዝርያ የሆኑ ዳልጋ ከብቶችን በጾታ በመለየት ብዛታቸውን በመጠይቁ በየጾታቸው ከተተወው ባዶ ቦታ መሙላት::

*ሠ3* *ጠቅላላ የተዳቀሉ ዝርያ ያላቸው*

በተራ ቁጥር 1 ከተመዘገቡት ጠቅላላ ፍየሎች የተዳቀለ ዝርያ ያላቸውን ብቻ በመለየት ጠቅላላ ብዛታቸውን በመጠየቅ በተሰጠው ክፍት ቦታ ይሞላል:: በመቀጠልም ድርጅቱ ካስመዘገባቸው ጠቅላላ የተዳቀሉ ዝርያ ያላቸውን በጾታ በመለየት ብዛታቸውን በመጠየቅ በየጾታው አንጻር በተተወው ባዶ ቦታ መመዝገብ ይገባል::

*የአሳማዎች ብዛት በዕድሜና በአገልግሎ ( የካቲት 1/1997 የነበሩትን )*

4. *ጠቅላላ የአሳማዎች ብዛት*

የካቲት 1/1997 ዓ.ም የመንግሥት ፣ የግል ንግድ፣የአምራቾች ህብረትና የሌሎች ድርጅት እርሻ የነበሩት ጠቅላላ የአሳማዎች ብዛትና እንዲሁም የወንድና የሴት ብዛት ተጠይቆ በአንጻራቸው በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይሞላል::

ሀ. *ከ6 ወር በታች*

በተራ ቁጥር 4 ከተመዘገቡት ጠቅላላ አሳማዎች ውስጥ ዕድሜያቸው 6 ወርና ከዚያ በላይ የሆኑት ጠቅላላ ብዛትና እንዲሁም የወንድና የሴት ቁጥር ድርጅቱን በመጠየቅ በአንጻራቸው በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይሞላል::

ለ1. <u>ለሥጋ አገልግሎት የሚውሉ</u>

ዕድሜያቸው 6 ወርና ከዚያ በላይ ከሆኑት አሳማዎች ውስጥ ለሥጋ አገልግሎት የሚውሉ አሳማዎቸ ጠቅላላ ብዛትና እንዲሁም በጾታ ድርጅቱን በመጠየቅ በአንጻራቸው በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይሞላል።

ለ2 <u>ለሌላ አገልግሎት የሚውሉ</u>

ዕድሜያቸው 6ወርና ከዚያ በላይ ከሆኑት አሳማዎች ውስጥ ለሌላ አገልግሎት የሚውሉ አሳማዎች ጠቅላላ ብዛትና እንዲሁም የወንድ እና የሴት ቁጥር ተጠይቆ በየአንጻራቸው በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይሞላል።

## <u>የፈረሶች አህዮች ፣ በቅሎዎችና ግመሎች ብዛት በዕድሜና በአገልግሎት (የካቲት 1/1997 ዓ.ም የነበሩትን)</u>

5. <u>ጠቅላላ የፈረሶች ብዛት</u>

የካቲት 1/1997 ዓ.ም ድርጅቱ የነበሩት ጠቅላላ የፈረሶች ብዛትና እንዲሁም የወንድና የሴት ቁጥር ድርጅቱን በመጠየቅ በአንጻራቸው በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይሞላል።

<u>ሀ)</u> <u>ከ3 ዓመት በታች</u>

በተራ ቁጥ 5 ከተመዘገቡት ጠቅላላ ፈረሶች ውስጥ ዕድሜያቸው ከሶስት ዓመት በታች የሆኑት ጠቅላላ ብዛት እና እንዲሁም በጾታ ተጠይቆ በአንጻራቸው በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይሞላል።

ለ) <u>3 ዓመትና ከ3 ዓመት በላይ</u>

በተራ ቁጥር 5 ከተመዘገቡት ጠቅላላ ፈረሶች ውስጥ ዕድሜያቸው ሶስት ዓመትና ከዚያ በላይ የሆኑት ጠቅላላ ብዛት እንዲሁም በጾታ ለይቶ በመጠየቅ በየጾታው አንጻር በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ይሞላል።

ለ1) <u>ለእርሻ አገልግሎት የሚውሉ</u>

ቁጥራቸው በ « ለ » ከተመዘገቡት ፈረሶች ውስጥ ድርጅቱ አብዛኛውን ጊዜ ለእርሻ ሥራ የሚጠቀምባቸው ጠቅላላ ብዛትና እንዲሁም በጾታ ለይቶ በመጠየቅ

ለ2) <u>ለሌላ አገልግሎት የሚውሉ</u>

ቁጥራቸው በ« ለ» ከተመዘገቡት ፈረሶች ውስጥ ድርጅቱ ለሌላ አገልግሎት የሚውሉ ያሏቸውን ጠቅላላ ብዛታቸውና እንዲሁም በጾታ ለይቶ በመጠየቅ በየጾታው አንጻር በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይሞላል። ለሌላ

አገልግሎት ሲባል ድርጅቱ በ«ለ1» ከእርሻ አገልግሎት ውጭ የሚጠቀምባቸውን ማለት ነው::

6. <u>ጠቅላላ የበቅሎዎች ብዛት</u>

የካቲት 1/1997 ዓ.ም ድርጅቱ የነበሩት ጠቅላላ በቅሎዎች ብዛትና እንዲሁም ብዛታቸውን በ ጾታ የወንድና የሴት ለይቶ ድርጅቱን በመጠየቅ በአንጻራቸው በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይሞላል::

ሀ) <u>ከ3 ዓመት በታች</u>

በተራ ቁጥር 6 ከተመዘገቡት ጠቅላላ በቅሎዎች ውስጥ ዕድሜያቸው ከሶስት ዓመት በታች የሆኑት ጠቅላላ ብዛት እና እንዲሁም በጾታ ተጠይቆ በአንጻራቸው በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይሞላል::

ለ) <u>3 ዓመትና ከ3 ዓመት በላይ</u>

በተራ ቁጥር 6 ከተመዘገቡት ጠቅላላ በቅሎዎች ውስጥ ዕድሜያቸው ሦስት ዓመትና ከዚያ በላይ የሆኑት ጠቅላላ ብዛትና እንዲሁም በጾታ ተጠይቆ በአንጻራቸው በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይሞላል::

ለ1) <u>አብዛኛውን ጊዜ ለእርሻ ሥራ የሚውሉ</u>

ቁጥራቸው በ«ለ» ከተመዘገቡት በቅሎዎች ውስጥ ድርጅቱ አብዛኛውን ጊዜ ለእርሻ ሥራ የሚጠቀምባቸው ጠቅላላ ብዛትና እንዲሁም በጾታ ተጠይቆ በአንጻራቸው በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይሞላል::

ለ2) <u>ለሌላ አገልግሎት የሚውሉ</u>

ቁጥራቸው በ«ለ» ከተመዘገቡት በቅሎዎች ውስጥ ድርጅቱ ለሌላ አገልግሎት የሚውሉ ያሏቸውን ጠቅላላ ብዛታቸውና እንዲሁም በጾታ ተጠይቆ በአንጻራቸው በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይሞላል::

7. <u>ጠቅላላ የአህዮች ብዛት</u>

የካቲት 1/1997 ዓ.ም ድርጅቱ የነበሩት ጠቅላላ አህዮች ብዛትና እንዲሁም የወንድና የሴት ቁጥር ባለይዞታውን በመጠየቅ በአንጻራቸው በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይሞላል::

ሀ) <u>ከ3 ዓመት በታች</u>

በተራ ቁጥር 7 ከተመዘገቡት ጠቅላላ አህዮች ውስጥ ዕድሜያቸው ከሶስት ዓመት በታች የሆኑት ጠቅላላ ብዛት እና እንዲሁም በጾታ ተጠይቆ በአንጻራቸው በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይሞላል::

ለ) <u>3 ዓመትና ከ3 ዓመት በላይ</u>

በተራ ቁጥር 7 ከተመዘገቡት ጠቅላላ አህዮች ውስጥ ዕድሜያቸው ሦስት ዓመትና ከዚያ በላይ የሆኑት ጠቅላላ ብዛት እና እንዲሁም በጾታ ተጠይቆ በአንጻራቸው በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይሞላል፡፡

ለ1 <u>ለእርሻ አገልግሎት የሚውሉ</u>

ቁጥራቸው በ «ለ» ከተመዘገቡት አህዮች ውስጥ ድርጅቱ አብዛኛውን ጊዜ ለእርሻ ሥራ የሚጠቀምባቸው ጠቅላላ ብዛትና እንዲሁም በጾታ ተጠይቆ በአንጻራቸው በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይሞላል፡፡

ለ2 <u>ለሌላ አገልግሎት የሚውሉ</u>

ቁጥራቸው በ« ለ» ከተመዘገቡት አህዮች ውስጥ ድርጅቱ ለሌላ አገልግሎት የሚውሉ ያሏቸውን ጠቅላላ ብዛታቸውና እንዲሁም በጾታ ተጠይቆ አንጻራቸው በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይሞላል፡፡

8. <u>ጠቅላላ የግመሎች ብዛት</u>

የካቲት 1/1997 ዓ.ም ድርጅቱ የነበሩት ጠቅላላ ግመሎች ብዛትና እንዲሁም የወንድና የሴት ቁጥር ድርጅቱን በመጠየቅ በአንጻራቸው በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይሞላል፡፡

ሀ) <u>ከ4 ዓመት በታች</u>

በተራ ቁጥር 8 ከተመዘገቡት ጠቅላላ ግመሎች ውስጥ ዕድሜያቸው ከአራት ዓመት በታች የሆኑት ጠቅላላ ብዛት እና እንዲሁም በጾታ ተጠይቆ በአንጻራቸው በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይሞላል፡፡

ለ) <u>ከ4 ዓመትና ከ4 ዓመት በላይ</u>

በተራ ቁጥር 8 ከተመዘገቡት ጠቅላላ ግመሎች ውስጥ ዕድሜያቸው አራት ዓመትና ከዚያ በላይ የሆኑት ጠቅላላ ብዛት እና እንዲሁም በጾታ ተጠይቆ በአንጻራቸው በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይሞላል፡፡

<u>ለ1 ለሥጋ አገልግሎት የሚውሉ</u>

ቁጥራቸው በ«ለ» ከተመዘገቡት ግመሎች ውስጥ ለሥጋ የሚውሉ ግመሎች ጠቅላላ ብዛትና እንዲሁም በጾታ ተጠይቆ በአንጻራቸው በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይሞላል፡፡

<u>ለ2 ለእርሻ አገልግሎት የሚውሉ</u>

ቁጥራቸው በ « ለ » ከተመዘገቡት ግመሎች ውስጥ ድርጅቱ አብዛኛውን ጊዜ ለእርሻ ሥራ የሚጠቀምባቸው ጠቅላላ ብዛትና እንዲሁም በጾታ ተጠይቆ በአንጻራቸው በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይሞላል፡፡

**ለ3) <u>ለወተት አገልግሎት የሚውሉ</u>**

**ቁጥራቸው በ«ለ» ከተመዘገቡት ግመሎች ውስጥ ድርጅቱ ወተት ይሰጡኛል ብሎ ያስቀመጣቸውን ግመሎች ብዛት ተጠይቆ በአንጻራቸው በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይሞላል::**

**ለ4) <u>ለሌላ አገልግሎት የሚውሉ</u>**

**ቁጥራቸው በ«ለ» ከተመዘገቡት ግመሎች ውስጥ ድርጅቱ ለሌላ አገልግሎት የሚውሉ ያሏቸውን ጠቅላላ ብዛታቸውና እንዲሁም በጾታ ተጠይቆ በአንጻራቸው በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይሞላል::**

## <u>ማስታወሻ:-</u>

***የእርሻ ሥራ ማረስን፣ መጠቅጠቅን ፣ መውቃትን ፣ እና ሌሎች ለእርሻ አጋዥ የሆኑ ሥራዎችን ያጠቃልላል::***

## <u>ፈረሶች፣ በቅሎዎችን ፣አህዮችን እና ግመሎችን በሚመለከት</u>

**<u>ለፈረሶች</u> :-**

**ተራ ቁጥር 4 = ሀ + ለ**

**ለ = ለ1 + ለ2 + ለ3**

***መሆኑን ማገናዘብ ያስፈልጋል::***

**<u>ለበቅሎዎች:-</u>**

**ተራ ቁጥር 5 = ሀ + ለ**

**ለ = ለ1 + ለ2 + ለ3**

***መሆኑን ማገናዘብ ያስፈልጋል::***

**<u>ለአህዮች</u> :-**

**ተራ ቁጥር 6 = ሀ + ለ**

**ለ = ለ1 + ለ2 + ለ3**

***መሆኑን ማገናዘብ ያስፈልጋል::***

**<u>ለግመሎች:-</u>**

**ተራ ቁጥር 7 = ሀ + ለ**

**ለ = ለ1 + ለ2 + ለ3 + ለ4+ ለ5**

***መሆኑን ማገናዘብ ያስፈልጋል::***

ዶሮዎች

9. የካቲት 1/ 1996 የነበሩ ጠቅላላ የዶሮዎች ብዛት

የካቲት 1/1996 ዓ.ም ባለይዞታው የነበሩት ጠቅላላ የዶሮዎች ብዛት ተጠይቆ በአንጻሩ በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይሞላል::

ሀ) ዕድሜያቸው ከ20 ሳምንት በላይ የሆኑ እንቁላል የሚጥሉ

በተራ ቁጥር 9 ከተመዘገቡት ጠቅላላ ዶሮዎች ውስጥ ዕድሜያቸው ከ20 ሳምንት በላይ ሆኖ እንቁላል የሚጥሉ እናት ዶሮዎች ( በጥናቱ ቀን እንቁላል ባይጥሉም ) ብዛታቸው ተጠይቆ በአንጻሩ በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይሞላል::

ለ) ዕድሜያቸው ከ20 ሳምንት በላይ የሆኑ እንቁላል የሚጥሉ

በተራ ቁጥር 9 ከተመዘገቡት ጠቅላላ ዶሮዎች ውስጥ ዕድሜያቸው ከ20 ሳምንት በላይ ሆኖ እንቁላል የማይጥሉ እናት ዶሮዎች ብዛታቸው ተጠይቆ በአንጻሩ በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይሞላል:: እንቁላል የማይጥሉ እናት ዶሮዎች ሲባል እንቁላል መጣል ያቆሙና ለእናትነት ደርሰው እንቁላል ጥለው የማያውቁትን መሆኑን ማስታወስ ያስፈልጋል::

ሐ) ዕድሜያቸው ከ20 ሳምንት በላይ አውራ ዶሮዎች

በተራ ቁጥር 9 ከተመዘገቡት ጠቅላላ ዶሮዎች ውስጥ ዕድሜያቸው ከ20 ሳምንት በላይ የሆኑ አውራ ዶሮዎች ብዛት ተጠይቆ በአንጻሩ በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይሞላል::

መ) ዕድሜያቸው ከ8-20 ሳምንት የሆናቸው ለአውራነት ያልደረሱ ዶሮዎች

በተራ ቁጥር 9 ከተመዘገቡት ጠቅላላ ዶሮዎች ውስጥ ዕድሜያቸው ከ8-20 ሳምንታት የሆኑ ለአውራነት ያልደረሱ ዶሮዎች ብዛት ተጠይቆ በአንጻሩ በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይሞላል::

ሠ) ዕድሜያቸው ከ8-20 ሳምንት የሆናቸው ቄብ ዶሮዎች

በተራ ቁጥር 9 ከተመዘገቡት ጠቅላላ ዶሮዎች ውስጥ ዕድሜያቸወ ከ8-20 ሳምንታት የሆኑ ቄብ ዶሮዎች ብዛት ተጠይቆ በአንጻሩ በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይሞላል::

ረ) ዕድሜያቸው ከ8 ሳምንት በታች የሆኑ ጫጩቶች

በተራ ቁጥር 9 ከተመዘገቡት ጠቅላላ ዶሮዎች ውስጥ ዕድሜያቸው ከ8 ሳምንት በታች የሆኑ ጫጩቶች ብዛት ተጠይቆ በአንጻሩ በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይሞላል::

__ማስታወሻ:-__

*ተራ ቁጥር ፱= ሀ+ ለ + ሐ + መ + ሠ + ረ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::*

**2.2** __ባለፉት 12 ወራት (ከየካቲት 2/1995-የካቲት 1/1997) የቤት እንስሳት ፣ ዶሮ ወይም የንብ ቀፎዎች ነበረዎት?__

አዎ = 1 አልነበረም = 2

የእርሻው መልስ አዎን ከሆነ ኮድ «1» በሣጥን ውስጥ ይሞላና ወደ ቀጣይ ጥያቄዎች መተላለፍ ያስፈልጋል:: የለም ካለ ደግሞ ኮድ «2» በሣጥኑ ውስጥ ተሞልቶ የጥያቄው መጨረሻ ይሆናል::

**10.** __ባለፉት 12 ወራት (ከየካቲት 2/199ፊ6-የካቲት 1/1997 ) ቢያንስ አንድ ጊዜ የማር ምርት የሰጡ ቀፎዎች ብዛት ?__

ድርጅቱ የካቲት 1/1997 ያሉት የንብ ቀፎዎች ( ባለፉት 12 ወራት ውስጥ ከየካቲት 2/1996- የካቲት 1/1997 ቢያንስ አንድ ጊዜ ማር የተመረተባቸው ቀፎዎች ) ብዛት ተጠይቆ በአንጻሩ በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ይሞላል::

**ሀ)** __ባህላዊ ቀፎዎች:-__

ከላይ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ማር የተመረተባቸው ባህላዊ ቀፎዎች ብዛት ተጠይቆ በአንጻሩ በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይሞላል::

**ለ)** __የሽግግር ወይም ባለመረባረብ ቀፎዎች__

ከላይ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ማር የተመረተባቸው መለስተኛ ዘመናዊ ቀፎዎች ብዛት ተጠይቆ በአንጻሩ በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይሞላል::

**ሐ)** __ዘመናዊ ቀፎዎች:-__

ከላይ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ማር የተመረተባቸው ዘመናዊ ቀፎዎች ብዛት ተጠይቆ በአንጻሩ በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይሞላል::

__ማስታወሻ:-__

*ባህላዊ ቀፎ ማለት ከተለያዩ ነገሮች (ለምሳሌ ከሸንበቆ፣ ከቀርከሃ ፣ከእንጨት፣ ከተከቦረቦረ ዛፍ ፣ከእንሥራ . . . ወዘተ የተሰራና ማር የሚመረትበት ማለት ነው::*

__የሽግግር ወይም ባለመረባረብ__ :- ማለት በግብርና ሚኒስቴር ወይም አግባብ ባላቸው መሥሪያ ቤቶች የሙያ ድጋፍ ተሠርቶ ከባህላዊ ቀፎ የተሻለ ምርት የሚሰጥ ማለት ነው::

__ዘመናዊ ቀፎ__:- ማለት በግብርና ሚኒስቴር ወይም አግባብ ባላቸው መሥሪያ ቤቶች የሙያ ድጋፍ ተሰርቶ ከፍ ያለ ምርት የሚሰጥ ማለት ነው::

## ባለፉት 12 ወራት ( ከየካቲት 2/1996 - የካቲት 1/1997 የተገኘ የወተት፣ የእንቁላልለ እና የማር ምርት መጠን

### 11. የወተት ላሞችና ግመሎች

ሀ. በዓመቱ ውስጥ ወተት የሰጡ ላሞች ብዛት

ድርጅቱ የካቲት 1/1997 ዓ.ም ከነበሩት ላሞች ውስጥ ባለፉት 12 ወራት ወተት ሲሰጡ የነበሩ ላሞች ብዛት ተጠይቆ በአንጻሩ በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባል::

ለ) በ«ሀ» ከተመዘገቡት ላሞች ውስጥ አንድ ላም በአማካይ በዓመቱ ለስንት ወራት ወተት ሰጠች

በ«ሀ» ከተመዘገቡት ላሞች ውስጥ አንድ ላም በአማካይ በዓመቱ በስንት ወራት ወተት እንደሰጠች በመጠየቅ ቁጥሩ በተዘጋጀው ባዶ ቦታ ይሞላል::

ሐ) በተለምዶ አንድ ላም በአማካይ ለስንት ወራት ትታለባለች (የተጠቀሰውን የጊዜ ገደብ ወይመለከትም ) የአለባ ወቅት በወራት

ድርጅቱ አንድ ላም በአማካይ ለስንት ወራት እንደምትታለብ ተጠይቆ (የአላባ ወቅት በወራት ) በአንቀጻሩ በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይሞላል::

መ) የወተት ምርት በቀን፣ በላም (በሊትር)

አንድ ላም በአማካይ በቀን ስንት ሊትር ወተት እንደበትሰጥ ድርጅቱ ተጠይቆ መጠኑ በሊትር በአንጻሩ በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባል::

ሠ) በዓመቱ ውስጥ ወተት የሰጡ ግመሎች ብዛት

ድርጅቱ የካቲት 1/1997 ዓ.ም ከነበሩት ግመሎች ውስጥ ባለፉት 12 ወራት ወተት ሲሰጡ የነበሩ ግመሎች ብዛት ተጠይቆ በአንጻሩ በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባል::

ረ) በ«ሠ» ከተከመዘገቡት ግመሎች ውስጥ አንድ ግመል በአማካይ በዓመቱ ውስጥ ለስንት ወራት ወተት ሰጠች

ድርጅት በ«ሠ» ከተመዘገቡት ግመሎች ውስጥ አንድ ግመል በአማካይ በዓመቱ ውስጥ ለስንት ወራት እንደሰጠች በመጠየቅ የወሩ ብዛት በተዘጋጀው ባዶ ቦታ ይመዘገባል::

ሰ) <u>በተለምዶ አንድ ግመል በአማካይ ለስንት ወራት ትታለባለች (የአላባ ወቅት በወራት)</u>

በተለምዶ አንድ ግመል በአማካይ ለስንት ወራት እንደምትታለብ ተጠይቆ የአላባ ወቅት በወራት በአንጻሩ በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይሞላሉ::

ሸ) <u>የወተት ምርት በቀን ግመል (በሊትር)</u>

አንድ ግመል በአማካይ በቀን ስንት ሊትር ወተት እንደበትሰጥ ባለይዞታው ተጠይቆ መጠኑ በሊትር በአንጻሩ በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባል::

<u>ማስታወሻ፡-</u>

*ድርጅቱ የወተቱን መጠን በአካባቢ መለኪያ የሰጠ እንደሆነ ውሀ በወተት ፋንታ ተተክቶ በሚዛን ተመዝኖ መሞላት አለበት :: (አንድ ሊትር ውሃ = አንድ ኪሎ ግራም ውሃ መሆኑ ይታወቅ)*

## 12. <u>የእንቁላል ምርት /ብዛት/ በዶሮ ( በአንድ መጣያ ወቅት )</u>

አንድ ዶሮ በአማካይ በአንድ የእንቁላል መጣያ ወቅት ስንት እንቁላል ልትጥል እንደምትችል ድርጅቱ ተጠይቆ በአንጻሩ በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይሞላል::

## 13. <u>አማካይ የእንቁላል መጣያ ወቅት ( በቀን )</u>

የአንድ ዶሮ አማካይ የእንቁላል መጣያ ወቅት ምን ያህል ቀኖች እንደሆነ ድርጅቱ ተጠይቆ በአንጻሩ በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባል::

**14.** ባለፉት 12 ወራት /ከየካቲት 2/1995-የካቲት 1/1997 ዓ.ም /በአማካይ የአንድ ዶሮ የእንቁላል መጣያ ወቅት ብዛት ምን ያህል እንደሆነ ባለይዞታው ተጠይቆ ይመዘገባል::

<u>ማስታወሻ</u>፡- *የሚጠየቀው የእንቁላል ብዛት በአንድ የእንቁላል መጣያ ወቅት ተጥሎ ድርጅቱ ለምግብነት ያዋለውን ፣ የተሸጠውን ፣ የተበላሸውን/የተሰበረውንና ወደ ጫጩትነት የተቀየረውን በሙሉ ያጠቃልላል::*

## 15. <u>የማር ምርት መጠን ( በኪ.ግ) በቀፎ በዓመት</u>

ሀ) <u>በአማካይ ከአንድ ባህላዊ ቀፎ የተገኘ የማር ምርት</u>

ድርጅቱ ከአንድ ባህላዊ ቀፎ በዓመት በአማካይ የሚያገኘው የማር ምርት መጠን በኪሎ ግራም እና በዓመቱ ውስጥ በአማካይ ከአንድ ባህላዊ ቀፎ ምን ያህል ጊዜ ምርት እንደሚያገኝ ተጠይቆ በየአንጻሩ በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይሞላል::

ለ) <u>በአማካይ ከአንድ ዘመናዊ ቀፎ የተገኘ የማር ምርት፡-</u>

ድርጅቱ ከአንድ ዘመናዊ ቀፎ በዓመት በአማካይ የሚያገኘው የማር ምርት መጠን በኪሎ ግራም እና በዓመቱ ውስጥ በአማካይ አንድ ዘመናዊ ቀፎ ምን ያህል ጊዜ ምርት እንደሚያገኝ ተጠይቆ በየአንጻሩ በተዘጋጁት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይሞላል፡፡

ሐ) <u>በአማካይ ከአንድ መለስተኛ ዘመናዊ ቀፎ የተገኘ የማር ምርት</u>

ድርጅቱ ከአንድ መለስተኛ ዘመናዊ ቀፎ በዓመት በአማካይ የሚያገኘው የማር ምርት መጠን በኪሎ ግራም እና በዓመቱ ውስጥ በአማካይ ከአንድ መለስተኛ ዘመናዊ ቀፎ ምን ያህል ጊዜ ምርት እንደሚያገኝ ተጠይቆ በየአንጻሩ ባሉት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይሞላል፡፡

## 16. <u>የቤት እንስሳት በሽታና ህክምናን በተመለከተ (ከየካቲት 2/1993-የካቲት 1/1994 ዓ.ም)</u>

<u>ዓምድ 1. ተራ ቁጥር</u>

የመስመር ተራ ቁጥር በዝርዝር ከ1 በመጀመር ተሰጥቷል፡፡

<u>ዓምድ 2. የቤት እንስሳት ዓይነት</u>

በዚህ ዓምድ የቤት እንስሳት ዓይነት የዳልጋ ከብቶች በጎች ፍየሎች የጋማ ከብቶች ግመሎች እና ዶሮዎች በመባል ተዘርዝረዋል፡፡ በዚህ ዓምድ ሥር ኮድ ተብሎ የተተወው ባዶ ቦታ ለቢሮ ሥራ ብቻ ስለሚያገለግል ምንም አይሞላበትም፡፡

<u>ዓምድ 3. ክትባት የተደረገላቸው ጠቅላላ ብዛት</u>

በዚህ ዓምድ ድርጅቱ ያስከተባቸውን ጠቅላላ የቤት እንስሳት ብዛት በየዓይነታቸው ተጠይቆ ተዘጋጅተው ባዶ ቦታ ውስጥ ይሞላል፡፡

<u>የተጠቁ ብዛት</u>

ድርጅቱ በዓምድ 3 በዓይነት ካስመዘገባቸው የቤት እንስሳት ውስጥ በበሽታ የተጠቁ ካሉ ብዛታቸው ተጠይቆ በተዘጋጀው ባዶ ቦታ ውስጥ ይሞላል፡፡

<u>ዓምድ5. ህክምና የተደረገላቸው ብዛት</u>

ድርጅቱ በዓምድ 4 በበሽታ የተጠቁ ብሎ በዓይነት ካስመዘገባቸው የቤት እንስሳት ውስጥ በባለሙያ እርዳታ የተደረገላቸው ካሉ ብዛታቸው ተጠይቆ በተዘጋጀው ቦታ ውስጥ ይሞላል፡፡

<u>ዓምድ 6. የሞቱ ብዛት</u>

በበሽታ ተጠቅተው የሞቱ የቤት እንስሳት ብዛት በየዓይነታቸው ተጠይቆ በተዘጋጀው ባዶ ቦታ ውስጥ ይሞላል፡፡

ማስታወሻ :- *1) ለዓምድ 3 ፣4 ፣5 እና 6 ለእያንዳንዳቸው ድምሩ መሞላት አለበት::*

*2) ዓምድ 3 ፣ የዓምድ 4፣ 5 እና 6 ድምር ውጤት ሊሆንም*

*/ላይሆንም እንደሚችል መገንዘብ ያስፈልጋል:*

## 17. የቤት እንስሳት መኖን በተመለከተ (ከየካቲት 2/1995-የካቲት 1/1996 ዓ.ም)

ዓምድ 1. ተራ ቁጥር

ተራ ቁጥር በዝርዝር ከ1 በመጀመር ተሰጥቷል::

ዓምድ 2. የመኖ ዓይነት

በዚህ ዓምድ የተለያዩ የመኖ አይነቶች ተዘርዝረዋል:: በዚህ ዓምድ ሥር ኮድ ተብሎ የተተወው ቦታ ለቢሮ ሥራ ብቻ ስለሚያገለግል ምንም አይሞላበትም::

ዓምድ 3. መኖ ተጠቅመዋል? ( አዎን ፣የለም)

ድርጅቱ በዓምድ 2 የተጠቀሰውን የመኖ ዓይነት መጠቀም አለመጠቀሙ ተጠይቆ መልሱ « አዎን» ከሆነ ኮድ «1» ÷ ያልተጠቀመ ከሆነ ደግሞ ኮድ «2» በተሰጠው ባዶ ሣጥን ውስጥ ይሞላል::

ዓምድ 4. አዎን ከሆነ ድርሻ በመቶኛ

በዓምድ 3 ኮድ «1» ለተሞላለት የመኖ ዓይነት አጠቃቀሙ በመቶኛ ሲሰላ ምን ያህል እንደሆነ ተጠይቆ በተሰጠው ባዶ ቦታ ውስጥ ይሞላል::

## ክፍል 3. የቤት እንስሳትና የንብ ተዋጽኦ መጠንና ዋጋ

ዓምድ 1. ተራ ቁጥር

ከ01 በመጀመር በቅደደብ ተከተል ተሰጥቷል::

ዓምድ 2. ዝርዝር

በዚህ ዓምድ የቤት እንስሳትና የንብ ተዋጽኦዎች በዝርዝር ተሰጥተዋል:: ምናልባት ከተዘረዘረው ውጭ ሌላ የተዋጽኦ ዓይነት ከተገኘ ሌላ በሚለው ቦታ ይገለጽና አስፈላጊው መረጃ ተጠይቆ ይሞላ:: በዚህ ዓምድ ኮድ ተብሎ በተዘጋጀው ባዶ ቦታ ለቢሮ ሥራ ብቻ ስለሚያገለግል ምንም አይሞላበትም ::

ዓምድ 3 መለኪያ

በዓምድ 2 ለተዘረዘረው የተዋጽኦ ዓይነት ለእያንዳንዱ የመለኪያ ስም ተጠይቆ በዚህ ዓምድ ሥር ይመዘገባል:: በዚህ ዓምድ ሥር ኮድ ተብሎ የተተወው ቦታ ለቢሮ ሥራ ብቻ ስለሚያገለግል ምንም አይሞላበትም::

ዓምድ 4 <u>የአንዱ ዋጋ</u>

በዓምድ 3 የተሞላው የመለኪያ ዓይነት አስመልክቶ ያንዱ መለኪያ ዋጋ (በተዋጽኦ ዓይነት) በብር ተጠይቆ በተሰጠው ክፍት ቦታ ውስጥ ይሞላል:: ምሣሌ በዓምድ 3 ኪሎ ግራም ተሞልቶ ከሆነ ያንዱ ኪሎ ግራም ዋጋ ( በተዋጽኦ ዓይነት) ተጠይቆ በብርና በሣንቲም በዚህ ዓምድ ሥር በተሰጡት ባዶ ቦታዎች ውስጥ ይሞላል ማለት ነው::

ዓምድ 5 እና 6. <u>ጠቅላላ ምርት</u>

ዓምድ 5. <u>መጠን</u>

ሰፋፊና መካከለኛ የመንግሥት /የግል ንግድና የአምራቾች ህብረት ሥራ ማህበር እርሻው ያለው ጠቅላላ ተዋጽኦ መጠን በዓምድ 2 በተዘረዘረው ተዋጽኦ ዓይነትና በዓምድ 3 በተጠቀሰው መለኪያ መሠረት ተጠይቆ መጠኑ በዚህ ዓምድ ሥር በተሰጡት ባዶ ቦታዎች ውስጥ ይሞላል::

ዓምድ 6. <u>ዋጋ</u>

ሰፋፊና መካከለኛ የመንግሥት /የግል ንግድና የአምራቾች ህብረት ሥራ ማህበር እርሻው ያለው ተዋጽኦ ጠቅላላ ዋጋ በብር በዓምድ 2 በተዘረዘረው የተዋጽኦ አይነት መሠረት በመጠየቅ በዚህ ዓምድ ሥር በተሰጡት ባዶ ባታዎች ውስጥ ይሞላል::

ዓምድ 7 እና 8. <u>በዓመቱ ውስጥ የተሸጡ</u>

ዓምድ 7. <u>ጠቅላላ መጠን</u>

ሰፋፊና መካከለኛ የመንግሥት /የግል ንግድና የአምራቾች ህብረት ሥራ ማህበር እርሻው የሸጠውን ጠቅላላ የተዋጽኦ መጠን በዓምድ 2 በተዘረዘረው የተዋጽኦ ዓይነትና በዓምድ 3 የተጠቀሰው መለኪያ መሠረት ተጠይቆ በዚህ ዓምድ ሥር በተሰጡት ባዶ ቦታዎች ውስጥ ይሞላል::

ዓምድ 8. <u>ጠቅላላ ዋጋ</u>

ሰፋፊና መካከለኛ የመንግሥት /የግል ንግድና የአምራቾች ህብረት ሥራ ማህበር እርሻው የሸጠው ተዋጽኦ ዋጋ በብር በዓምድ 2 በተዘረዘረው የተዋጽኦ ዓይነት መሠረት በመጠየቅ በዚህ ዓምድ ሥር በተሰጡት ባዶ ቦታዎች ውስጥ ይሞላል::

ዓምድ 9. <u>የተበላሸ ተዋጽኦ መጠን</u>

ሰፋፊና መካከለኛ የመንግሥት /የግል ንግድና የአምራቾች ህብረት ሥራ ማህበር እርሻው በአያያዝ ጉድለት ወይም በሌሎች ምክንያቶች ከማንኛውም ዓይነትና በዓምድ 3 በተጠቀሰው መለኪያ መሠረት በመጠየቅ በዚህ ዓምድ ሥር በተሰጡት ባዶ ቦታዎች ውስጥ ይሞላል፡፡

ዓምድ 10. <u>በዓመቱ ውስጥ ሳይሸጥ የቀረ ተዋጽኦ መጠን</u>

የሰፋፊና መካከለኛ የመንግሥት /የግል ንግድና የአምራቾች ህብረት ሥራ ማህበር እርሻው በዓመቱ ውስጥ ሳይሸጡ የቀሩና በመጋዘን ወይም በሌላ ቦታ ያስቀመጣቸው ተዋጽኦዎች ጠቅላላ መጠን በዓምድ 2 በተዘረዘረው በተዋጽኦ ዓይነትና በዓምድ 4 በተጠቀሰው መለኪያ መሠረት ተጠይቆ በዚህ ዓምድ ሥር በተሰጡት ባዶ ቦታዎች ውስጥ ይሞላል፡፡

## <u>አስተያየት</u>

*ይህ ዓምድ በተለለይ የተበላሹ ተዋጽኦዎች የተበላሹበት ምክንያት የሚገለጽበት ሲሆን በተጨማሪም ክፍል 7ን በሚመለከት ሌሎች የገጠሙ ችግሮችና ሌሎች አስተያየቶች ካሉ ይገልጹበታል፡፡*